# መጻሕፍተ ብሉያት ሠለስቱ

## እሉ እሙንቱ

- ኢያሱ
- መሣፍንት
- ሩት

አሳታሚ :-
ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

ሰኔ 2000 ዓ.ም.
አዲስ አበባ፣
ኢትዮጵያ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ

ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኵሱም፣

ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ፕሬዝዳንት ዘዓለም አብያተ ክርስቲያናት፣

የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት

# <u>መግለጫ</u>

**ጌታ በወንጌል « እስመ ኢኮንክሙ አንትሙ ዘትትናገሩ አላ መንፈሱ ለአቡክሙ ለማያዊ ውእቱ ይትናገር በላዕሌክሙ» (ማቴ ፲፥፳) ሲል እንደተናገረው ቅዱሳት መጻሕፍት በሙሉ በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፉ በመሆናቸው « መጻሕፍት አምላካውያት » ይባላሉ:: ፍ.ነገሥት አንቀጽ ፪)**

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ ሐዲሳት ቍጥር ፹፩ ሲሆን ከአምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ ቀጥሎ ሦስቱ የኢያሱ፣ የመሳፍንትና የሩት መጻሕፍት በተከታታይ ዘመን የተጻፉና የተነገሩ ናቸው::

በመሆኑም አንዱ የሌላውን ፍጻሜ ይናገራል፤ የእግዚአብሔር አገልጋይና የእስራኤል ሕዝብ መሪ ሙሴ ከሞተ በኋላ ኢያሱ በሙሴ እግር ተተክቶ ከአሪት ዘዳግም በኋላ ያለውን ታሪክ ይቀጥላል:: (ኢያሱ ፩፥፩-፱)

መጽሐፈ መሳፍንትም ኢያሱ ከሞተ በኋላ ያለውን የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ በቀጣይነት ይዞ ይገኛል:: (መሳ. ፩፥፩)

እንደዚሁም መጽሐፈ ሩት በዘመነ መሳፍንት የተፈጸመውን ድርጊት ስለሚተርክ የመጽሐፈ መሳፍንት ተከታታይ ወይም የአንድ ዘመን ታሪክ ነው:: (ሩት ፩፥፩)

<u>የዘመናቸውም ቅደም ተከተል</u> :-

- ኢያሱ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ፲፬፻፶፩
- መሳፍንት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ፲፬፻፳፭
- ሩት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ፲፫፻፳፪ ነው::

እነዚህ ሦስት መጻሕፍት በግእዝና በሰብዓ ሊቃናት ቀኖና ከአምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ ጋር ተዳምረው ስምንቱ ብሔረ ኦሪት እየተባሉ ይጠራሉ ፤ ይህም ከሕጉ ጋር ፤ በተከታታይ በመነገራቸውና እርስ በእርስ በመያያዛቸው ነው ::

በሌላ በኩል ግን ሦስቱ የኢያሱ፣ የመሳፍንትና የሩት መጻሕፍት በይዘታቸው የታሪክ መጻሕፍት ናቸው::

በአይሁድ ቀኖና ደግሞ ሁለቱ የኢያሱና የመሳፍንት መጻሕፍት ከቀደምት ነቢያት ጋር ሲመደቡ፣ መጽሐፈ ሩት ግን ከአምስቱ ጥቅልሎች ጋር ይመደባል::

<u>አምስቱ ጥቅልሎች የሚባሉትም</u>:-

- መጽሐፈ ሩት፣
- መጽሐፈ መሐልየ መሐልይ፣
- መጽሐፈ ሰቆቃወ ኤርምያስ፣
- መጽሐፈ አስቴር፣
- መጽሐፈ መክብብ ናቸው::

## ፩ <u>መጽሐፈ ኢያሱ</u>:-

የኢያሱ መጽሐፍ ከሙሴ ሞት በኋላ የተፈጸመውን የታሪክ ዝርዝር ይገልጣል ፤ ምድረ ከንዓንን ለመያዝ የተደረገውን ዝግጅትና እስራኤል ምድሪቱን መካፈላቸውን ያስረዳል:: በመጨረሻም ኢያሱ ሕዝቡ አምልኮተ እግዚአብሔርን እንዳይተው ቃል ኪዳን ማስገባቱንና ምስክር እንዲሆንባቸውም ሐውልተ ስምዕ ማቆሙን ይናገራል:: (ኢያሱ ፳፬፥፳፯)

## ፪ <u>መጽሐፈ መሳፍንት</u>:-

መጽሐፈ መሳፍንት የመጽሐፈ ኢያሱ ቀጣይ ታሪክ ሲሆን፣ ጸሐፊውም ሳሙኤል እንደ ነበር ምሁራን አሪት ይጽፋሉ ፤ በዘመነ መሳፍንት ማእከላዊ አመራር አልነበረም::

ስለዚህም በየጊዜው ጠላት እየተነሳ እስራኤልን ያጠቃቸው ነበር፤ ያንጊዜም ወደ እግዚአብሔር ሲጮሁ ከመካከላቸው መስፍን ያስነሳላቸው ነበር ፤ መሳፍንት እንደ ነገሥታት ሐረግ ምስፍና አልነበራቸውም ፤ ከማንኛውም ነገደ እስራኤል መስፍን ሊነሣ ይችል ነበር ፤ ዘመነ መሳፍንት አራት መቶ አምሳ ዓመት ያህል ሲሆን፣ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ዐሥራ አራት መሳፍንት በየተራ ሕዝበ እስራኤልን መርተዋል::(የሐዋ ፲፫፥፳) መሳ. ከምዕራፍ ፫፥፲፫ ምዕራፍ ያለውን ይመለከቷል::

## ፫ <u>መጽሐፈ ሩት</u>

በሦስት ሴቶች ስም ከሚጠሩት መጻሕፍት ውስጥ አንዱ መጽሐፈ ሩት ነው ፤ ሩት ሞአባዊት ስትሆን በእምንትና አይሁዳዊውን

ቦኤዝን በማግባት አይሁዳዊት ሆናለች ፤ በዚህም ምክንያት ለእስራኤል ንጉሥ ለዳዊት ቅርብ አያት ስትሆን፣ ለእስራኤል ዘነፍስ መንፈሳዊ ንጉሥ ለሆነው ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢያሱስ ክርስቶስ ደግሞ በሥጋ ሩቅ ቅድመ አያት ሆናለች።(ማቴ፩፥፭)

እነዚህ ሦስት መጻሕፍት መጀመርያ ወደ ግእዝ ተተርጕመው በግእዝ ሲነበቡና ሲብራሩ ኖረዋል ፤ በኋላም በአማርኛ የአንድምታ ትርጓሜ በተዘጋጀ ጊዜ ለእነዚህም መጻሕፍት የአንድምታ ትርጓሜ ተዘጋጅቶላቸው፣መምህራን በቃል ሲያስተምሩአቸው፣ደቀመዛሙርትም በቃላቸው ሲያጠኑአቸው ኖረዋል ፤ አንዳንድ መምህራንና ደቀ መዘመርትም መጻሕፍቱን ለመጻፍ ሲሞክሩ ሁኔታው ምቹ ካለመሆኑ የተነሣ ንባቡንና ትርጓሜውን አሟልተው ለመጻፍ አይችሉም ነበር።

ስለሆነም ንባቡን በምሕፃር (በምልክት) ጽፈው ትርጓሜውን በሙሉ ለመጻፍ ይገደዱ ነበር ፤ይህ ሁኔታ እስከጊዜያችን ደርሶአል።

እነሆ አሁን ግን ይህ ችግር እንዲወገድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሙሉ ንባባቸው ከትርጓሜያቸው ጋር ከጥንት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው የአንድምታ ትርጓሜ ዘይቤ መሠረት ተዘጋጅቶ በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅታችን በኩል እንዲታተም አድርገናል።

«እስመ ኵሉ እምኔሁ፣ ወኵሉ በእንቲአሁ፣
ወኵሉ ቦቱ፣ ወሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም»
( ሮሜ ፲፩ ፴፮)

አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ፣
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዝዳንትና፣
የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝደንት

| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| ኢያሱ | ፩ ÷ ፻፳ |
| መሣፍንት | ፩ ÷ ፻፳ |
| ሩት | ፩ ÷ ፲፯ |

# ኦሪት ዘኢያሱ

ዜና ዘኢያሱ ሲል ነው ፤

ኢያሱ ማለት መድኃኒት ማለት ነው ፤ ኢሳይያስ ኢየሱስ ማለት መድኃኒት ማለት እንደሆነ የኢያሱን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው ፤ ይህ አርእስት ነው ፤ ሠለስቱ ምዕት ለመጻሕፍት አርእስት ሲሰጡ አርእስት ሰጥተውታል፤ እርሱ ግን ነገሩን ወከነ እም ድኅረ ሞተ ሙሴ ብሎ ይጀምራል ።

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ወከነ እምድኅረ ሞተ ሙሴ ገብረ እግዚአብሔር ይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ወልደ ነዌ ላእኩ ለሙሴ ፤

የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ ከሞተ በኋላ እንዲህ ሆነ፤ እግዚአብሔር የሙሴ አገልጋይ የሚሆን የነዌ ልጅ ኢያሱን እንዲህ አለው ፤ ከነ ያለውን ይቤሎ ብሎ ገለጸው ፤

፪፤ ወናሁ ሞተ ሙሴ ቀሥልዔየ ወይእዜኒ ተንሥእ ወእድዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ አንተ ወኵሉ ዝንቱ ሕዝብ ውስተ ምድር እንተ እሁበ ክሙ አነ ለክሙ ለደቂቀ እስራኤል ፤

እነሆ ወዳጄ ሙሴ ሙቷል ፤ አሁንም አንተ ተነሥተህ ይህን ዮርዳኖስን ተሻገረው ፤ ለናንተ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ እኔ ወደምሰጣችሁ አገር ለመሔድ ሕዝቡም ሁሉ ይሻገሩት ፤

፫፤ ኵሉ መካነ ነበ ኬዳ እገሪክሙ ለክሙ ነዋ እሁበክሙ በከመ እቤሎ ለሙሴ ፤

ለሙሴ እንደነገርኩት እግራችሁ የረገጠውን ቦታ ሁሉ እነሆ ለናንተ እሰጣችኋለሁ ፤

፬፤ እምገዳም ዘአንጢሊባኖስ እስከ ፈለግ ዓቢይ ፈለገ ኤፍራጥስ ኵሉ ምድሮሙ ለኬጥያውያን ፤

በአንጢሊባኖስ ካለው ምድረ በዳ ጀምሮ ኤፍራጥስ እስከ ሚባለው ወንዝ ድረስ የኬጥ ያውያንን አገር ሁሉ አወርሳችኋለሁ ፤

ወእስከ ደኃሪት ባሕር ወእስከ ምዕራብ ፀሐይ ይኩን ደወልክሙ ፤

አውራጃችሁም (ወሰናችሁ) እስከ ኤርትራ ድረስና በፀሐይ መግቢያ እስካለው አገር ድረስ ይሁንላችሁ ፤

፭፤ ወአልቦ ሰብእ ዘይትቃወም ቅድሜከ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትከ ፤

በሕይወት በምትኖርበት ዘመን ሁሉ አንተን የሚቃወም የለም፤

ወበከመ ሀሎኩ ምስለ ሙሴ ከማሁ እሄሉ ምስሌከ ወኢየኀድገከ ወኢይትዔወረከ ፤

ከሙሴ ጋር በረድኤት እንደ ኖርኩ ካንተም ጋር በረድ

ኤት እኖራለሁ ፤ በመከራ አልጥልህም ቸል አልልህም ።

፮፤ ጽናእ ወትባእ እስመ አንተ ትከፍሎሙ ለዝንቱ ሕዝብ ምድረ እንተ መሐልኩ ለአበዊሆሙ ከመ አሀቦሙ ፤

እሰጣችው ዘንድ ላባቶቻቸው የማልኩላቸውን ምድረ ርስት አንተ ለኒህ ወገኖች ታወርሳቸዋለህና ጽና በርታ ።

፯፤ ወባሕቱ ጽናእ ወትባእ ጥቀ ከመ ትዕቀብ ወትግበር ኵሎ ሕገ ዘከመ አዘዘከ ሙሴ ቍልዔየ ፤

ነገር ግን ወዳጄ ሙሴ እንዳዘዘህ ሕጉን ትጠብቅ ዘንድ ሥርዓቱንም ሁሉ ትሠራ ዘንድ ፈጽመህ ጽና በርታ ።

ወኢትትገኆሥ እምኔሁ ኢለየማን ወኢለጸጋም ከመ ታእምር ኵሎ ዘከመ ትገብር ፤

የምትሠራውን ሁሉ አውቀህ ትሠራ ዘንድ፤ ወደቀኝም ሁኖ ወደግራም ሁኖ ፈቅ አትበል፤ ቀኙን ጠልቶ አይደለም፤ ግራን ሲያይ ነው እንጂ ። አንድም ቀኝ መስሎ የሚሠራ ክፉ ሥራ አለና ።

፰፤ ወኢትትነደግ መጽሐፉ ለዝንቱ እምአፉከ ወአንብብ ቦቱ መዓልተ ወሌሊተ ከመ ታእምር ኵሎ ገቢረ ዘጽሑፍ ውስቴቱ እስመ ትረትዕ ፍኖትከ ወቦቱ ትጠበብ ፤

ይህንን መጽሐፍ ካንደበትህ አትለየው በውስጡ የተጻፈውን በሥራ ታውቅ ዘንድ በመዓልትም በሌሊትም ተመልከተው ሥራህ የቀናች ትሆናለችና እሱንም በመመልከት አዋቂ ትሆናለህና ።

፱፤ ወናሁ እኤዝዘከ ትባእ ወጽናእ ወኢትፍራህ ወኢትደንግፅ እስመ ሀለወ እግዚአብሔር አምላክከ ምስሌከ ውስተ ኵሉ ዘሖርከ ፤

እነሆ ጽና በርታ አትፍራ ፤ አትደንግጥ ብዬ አዝዝሀለሁ ፤ ፈጣሪህ እግዚአብሔር በሔድክበት ሁሉ ካንተ ጋር በረድኤት አለና ።

፲፤ ወአዘዞሙ ኢያሱ ለጸሐፍተ ሕዝብ ወይቤሎሙ ባኡ ውስተ ትዕይንት ወአዝዝዎሙ ለሕዝብ ወበልዎሙ አስተዳልዉ ለክሙ ስንቀ ፤

ኢያሱም በሕዝቡ ላይ የተሾሙትን ሹማምንቱን እንዲህ ብሎ አዘዛቸው ፤ ወደሠፈሩ ገብታችሁ ለመንገድ የሚሆናችሁ ስንቃችሁን አዘጋጁ ብላችሁ ሕዝቡን እዘዟቸው ።

፲፩፤ እስመ እስከ ሠለስ መዋዕል ተዐድውዎ ለዝንቱ ዮርዳኖስ አንትሙ ወትበውኡ ምድረ እንተ

ይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክ አበዊክሙ ከመ ትትዋረስዋ ፤

እናንተ ይህንን ዮርዳኖስን እስከ ሦስት ቀን ድረስ ተሻግራችሁ ትወርሷት ዘንድ ያባቶቻችሁ ፈጣሪ እግዚአብሔር ወደሚሰ ጣችሁ አገር ትገባላችሁና ስን ቃችሁን አዘጋጁ በሏቸው ፤

፲፪፤ ወለሮቤልሂ ወለጋድ ወለመ ንፈቀ ነገደ ምናሴሂ ይቤሎሙ ኢያሱ ፤

ነገደ ሮቤልንና ነገደ ጋድን የምናሴንም ነገድ እኩሌታ ኢያሱ እንዲህ አላቸው ፤

፲፫፤ ተዘከሩ ቃለ ዘአዘዘክሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር ወይቤ ለክሙ ናሁ አዕረፈክሙ እግዚአ ብሔር ለክሙ ወወሀበክሙ ዘተ ምድረ ፤

የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ ያዘዛችሁን ነገር አስቡ፤ እነሆ እግዚአብሔር ከመከራው አሳ ርፎ ይችን አገር አወረሳችሁ ብሎ የነገራችሁን አስቡ ፤

፲፬፤ ወይንበሩ አንስቲያክሙ ወደ ቂቅክሙ ወእንስሳክሙ ውስተ ዛቲ ምድር ዘወሀበክሙ ሙሴ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤

ሚስቶቻችሁና ልጆቻችሁ ከብ ቶቻችሁም ሁሉ እግዚአብሔር በሙሴ አድሮ በዮርዳኖስ ማዶ ባወረሳችሁ አገር ይቀመጡ ፤

ወአንትሙሰ ዕድዉ ዮርዳኖስ ቅኑታ ኒክሙ ቅድመ አኃዊክሙ ኵሉ ጽኑ ዓኒክሙ ወተቃተሉ ሎሙ ፤

እናንተ ግን አርበኞቹ ሁሉ የጦር መሣሪያችሁን ታጥቃችሁ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ለወን ድሞቻችሁ ተዋጉላቸው ፤

፲፭፤ እስከ አመ ያዐርፎሙ እግዚ አብሔር አምላክነ ለአኃዊክሙ ከማ ክሙ ወይወርሱ እሙንቱኒ ምድ ሮሙ እንተ ይሁቦሙ እግዚአብ ሔር አምላክነ ፤

ወንድሞቻችሁን እንደናንተ እግ ዚአብሔር ከመከራው እስኪ ያሳርፋቸው ድረስ ተዋጉላ ቸው ፤ እነርሱም ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ምድረ ርስት ይወርሳሉ ፤

ወተአትዉ እንከ አሐዱ አሐዱ እም ኔክሙ ውስተ ርስትክሙ ወትወር ስዋ አንትሙ ለዛቲ ምድር ዘወሀበ ክሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብ ሔር በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ምሥራቀ ፀሐይ ፤

ከዚህ በኋላ ከናንተ አንዱም አንዱም ወደርስታችሁ ተመ ልሳችሁ የእግዚአብሔር ባለ ሟል ሙሴ በፀሐይ መውጫ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ ያወረ ሳችሁን ምድረ ርስት ወርሳ ችሁ ትኖራላችሁ ፤

፲፯፤ ወአውሥእዎ ለኢያሱ ወይቤልዎ ንገብር ኵሎ ዘአዘዝከነ ወነሐውር መካነ ኀበ ፈነውከነ ፤

እነርሱም ለኢያሱ መለሱለት፤ እንዲህ አሉት ፤ ያዘዝኸንን ሁሉ እናደርጋለን፤ ወደምትልከን ቦታም እንሔዳለን ፡

፲፰፤ ወበከመ ተአዘዝነ ለሙሴ በኵሉ ከማሁ ንትኤዘዝ ለከ፡ ወባሕቱ ምስሌከ፡ የሃሉ እግዚአብሔር በከመ ሀለወ ምስለ ሙሴ ፤

ለሙሴ እንደታዘዝነ ለአንተም እንታዘዛለን ነገር ግን እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በረድኤት እንደኖረ ካንተም ጋር በረድኤት ይኑር ማለት በሙሴ አድሮ ጠላቶቻችንን ድል እንደነሣልን ባንተም አድሮ ድል ይንሣልን ፡

፲፱፤ ወብእሲ ዘኢተአዘዘ ለከ ወዘክሕደከ ወዘኢሰምዐ ቃለከ ዘአዘዝካሁ ለይሙት ወይእዜኒ ጽናእ ወትባእ ፤

ለአንተ የማይታዘዝ አንተን የካደ (አሌ ያለህ) ፤ ያዘዝከውንም ቃል ያልሰማ ሰው ሁሉ በድንጊያ ተወግሮ ይሙት ፤ አሁንም ጽና በርታ አሉት ።

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወፈነወ ኢያሱ እምሰጢን ፪ተ ወራዙተ ሰብአ ዓይን ጽሚተ ወይቤ ሎሙ ዕርጉ ወረአይዋ ለይእቲ ምድር ወለኢያሪኮሂ ፤

ኢያሱ በሰጢን ሠፍሮ ሳለ ሁለት ጒበኞችን ላከ ፤ ወጥታችሁ ያችን አገር ኢያሪኮንም ሰልላችሁ አይታችሁ ኑ አላቸው ፡

ወሐሩ እልክቱ ፪ቱ ወራዙት ወበጽሑ ኢያሪኮ ወቦኡ ውስተ ቤተ አሐቲ ብእሲት ዘማ እንተ ስማ ረዓብ ወኀደሩ ህየ ፤

እነዚያም ሁለቱ ጒበኞች ከዚያ ተነሥተው ሔደው ኢያሪኮ ደረሱ፤ ስሟ ረዓብ ወደምትባል ወደ አንዲት ዘማ ሴት ቤት ገብተው በዚያ አደሩ ፡ (ሐተታ) ይህች ረዓብ የምትቀበል ነገሥታቱን መኳንንቱን ነው ያሉ እንደሆነ ፪ቱን ቅጽር ገብታ ከ፫ኛው ወደ ውጭ ዛኒጋባ ሠርታ ትኖር ነበር ፤ የምትቀበል ሕዝቡን ነው ያሉ እንደሆነ አንዱን ቅጽር ገብታ ፪ቱን ወደውስጥ አድርጋ ከዚያ ከ፫ኛው ዛኒጋባ ጥላ ትኖር ነበረ ፡

፪፤ ወአይድእዎ ለንጉሠ ኢያሪኮ ወይቤልዎ ናሁ ቦኡ ዝየ ዕደው በሌሊት እምደቂቀ እስራኤል ሰብአ ዓይን ከመ ይርአዩ ብሔረነ ፤

ለኢያሪኮ ንጉሥ አገራችንን ይሰልሉ ዘንድ ከእስራኤል ልጆች

ጕብኞች ሰዎች በሌሊት ወደ
ከተማችን ገቡ ብለው ነገሩት ፤
(ሐተታ) በምን አውቀው ቢሉ
እንግዳ ሰው በዓይኑ ይታወ
ቃልና የጕብኛ ዓይኑ ባካና
እንዲሉ ፤ አንድም እስራኤል
ቅርጸ ቀላሎች ልብሰ ነጫጮች
ናቸው ፣ አሕዛብ ግን ልብሰ
አዳፋ ቁመተ ገፋፋ ናቸውና ፤
አንድም እስራኤል ዮርዳኖስን
መሻገራቸው ታውቋል ተሰም
ቷልና ፤

፫፤ ወለአከ ንጉሠ ኢያሪኮ ኀበ ረዓብ
ዘማ ወይቤ በልዋ ለረዓብ አውፅኢ
ዕደወ እለ ቦኡ ኀቤኪ ሰብአ ዓይን
እሙንቱ ከመ ይርአዩ ብሔረነ
መጽኡ ፣

የኢያሪኮ ንጉሥም ወደ ረዓብ
ዘማ ላከ ፣ ከቤትሽ የገቡ ሰዎች
የሀገራችንን መውጫ መግቢ
ያውን ሊያዩ የመጡ ጕብኞች
ናቸውና ከቤትሽ አውጭ ብሎ
ላከ ፤

፬፤ ወነሥአቶሙ ይእቲ ብእሲት
ለእልክቱ ፪ቱ ዕደው ወኀብአቶሙ
ወትቤ ዕደውሰ ቦኡ ኀቤየ ወኢያእ
መርኩ እምአይቴ እሙንቱ ፣

ያችም ሴት እነዚያን ሁለቱን
ሰዎች ወደ ሰገነት አውጥታ ሠወ
ረቻቸው ፣ እንዲህም አለች ፣
መግባትስ ገብተው ነበር የሔ
ዱበትን ግን አላወቅሁም ፤

፭፤ ወእንዘ ዕፁው ኆኅት ወበጽል
መት ወጽኡ ውእቶሙ ዕደው ወኢ
ያእመርኩ አይቴ እንከ ሖሩ ፣

በጨለማ ገብተው ደጅ ተዘ
ግቶ ሳለ በሌሊት ወጥተው
ሔዱ ከየት እንደመጡ ወዴ
ትም እንደ ሔዱ ግን አላወ
ቅሁም ፤

ወሑሩ እንከ ፍጡነ ትልውዎሙ
ወዴግንዎሙ የጊ ትረክብዎሙ ፣

ፈጥናችሁ ሒዳችሁ ተከተሏ
ቸው ፣ ወይም ታገኟቸው ይሆ
ናል አለቻቸው ፣ መግባታቸ
ውን አመነች ፣ መሔዳቸውን
እንዲያምኑላት ፤

፮፤ ወይእቲሰ አዕረገቶሙ ውስተ
ናሕስ ወኀብአቶሙ ማዕከለ ዕፀው
ውስተ ኀለት ዘውጡሕ ፣

እሷ ግን ወደ ሰገነት አውጥታ
በተከመረ እንጨት መካከል
በቅርቅህ አቴና ጠቅልላ አቆ
መቻቸው ፤

፯፤ ወዴገንዎሙ ውእቶሙ ዕደው
እንበለ ይቢቱ ፣

መግባታቸውን ብታምንላቸው
መሔዳቸውን አምነውላት ሳያ
ድሩ (ገብተን እንይ ሳይሉ)
ወዲያው ተከተሏቸው ፤

፰፤ ወይእተ ጊዜ ዐርገት ኀቤሆሙ
ውስተ ናሕስ ወትቤሎሙ አእምር

ከመ እግብእ እግዚአብሔር ለብ
ሔርነ ለክሙ ፤

ያን ጊዜም ወደሰገነቱ ወጥታ
እንዲህ አለቻቸው ፤ እግዚአብ
ሔር አገራችንን በናንተ እጅ
እንዲጥላት አውቃለሁ ፡፡

፱፡ እስመ አምጽአ እግዚአብሔር
ፍርሃተክሙ ላዕሌነ ወተመስዉ
ኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ብሔር
እምገጽክሙ ፤

እግዚአብሔር መፍራታችሁን
በኛ ላይ አምጥቶብናልና ፤ በሀ
ገር የሚኖሩ ሰዎችም ሁሉ እና
ንተን ከመፍራት የተነሣ እንደ
ሰም ቀልጠዋልና ፡፡

፲፡ እስመ ሰማዕነ ከመ አይበሳ እግ
ዚአብሔር ለባሕረ ኤርትራ እም
ቅድመ ገጽክሙ አመ አውፅአክሙ
እምድረ ግብፅ ፤

እግዚአብሔር ከግብፅ ባወጣ
ችሁ ጊዜም ኤርትራን ከፊት
ካራት ከፍሎ እንዳሻገራችሁ
ሰምተናልና ፡፡

ወኵሎ ዘገብረ ላዕለ ነገሥተ አሞ
ሬዎን እለ ሀለዉ ማዕዶተ ዮርዳ
ኖስ ለሴዎን ወለአግ እለ ሠረውክ
ምዎሙ ፤

በዮርዳኖስ ማዶ ባሉ እናንተ
ባጠፋችኋቸው በአሞሬዎን ነገ
ሥታት በሴዎንና በአግ ላይ
ያደረገውን ታምራት ሁሉ ሰም
ተናልና ፡፡

፲፩፡ ወሶበ ሰማዕነ ንሕነ ደንገጸ ልብነ
ወኢተርፈ ነፍሰ ፩ዱ እምኔነ እምቅ
ድመ ገጽክሙ ፤

እኛም የተደረገውን ታምራት
በሰማን ጊዜ ልቡናችን ተሸበረ
ብን ፤ ያንድ ሰው ልቡና እን
ኳን ከመፍራት የቀረ የለም ፡፡

እስመ እግዚአብሔር አምላክክሙ
ውእቱ አምላክ በሰማይ በላዕሉ ወበ
ምድር በታሕቱ ፤

ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ከም
ድር በላይ ባለ በሰማይ ፤ ከሰ
ማይ በታች ባለ በምድር እው
ነተኛ ፈጣሪ ነውና ፡፡

፲፪፡ ወይእዜኒ መሐሉ ሊተ በእግ
ዚአብሔር በከመ ገበርኩ ምስሌ
ክሙ ምሕረተ ከመ ትግበሩ ምስ
ሌየ ምሕረተ ወምስለ ቤተ አቡየ
ወተሀቡኒ ተአምረ በጽድቅ ፤

አሁንም እኔ ለእናንተ በጎ እን
ዳደረግሁላችሁ እናንተም ለኔ
ላባቴም ወገኖች ሁሉ በጎ ነገር
እንድታደርጉ ፤ የምድንበትንም
ምልክት እንድትነግሩኝ በእግ
ዚአብሔር ማሉልኝ ፡፡

፲፫፡ ወአሕይዉ ቤተ አቡየ ወእ
ምየኒ ወአኃውየኒ ወኵሎ ቤትየ

ወኵሎ ዘዚአሆሙ አድኅኑ ነፍስነ እሞት ፤

ያባቴንና የናቴን ወገን ወንድሞቼን ገንዘቤንና ገንዘባቸውን ሁሉ ሰውነታችንንም ሁሉ ከጥፋት አድኑ (እንድታድኑ ማሉልኝ አለቻቸው) ፤

፲፬፤ ወይቤልዋ እሙንቱ ዕደው ነፍስነ ህየንቴክሙ ውስተ ሞት ወትቤሎሙ ይእቲ አመ አግብአ እግዚአብሔር ለሀገርነ ውስተ እደዊክሙ ግበሩ ምሕረተ ወጽድቀ ምስሌየ ፤

እነሱም ጠንቅቀው ይምሉላታል ፤ ይህን ምሥጢር ካላወጣሽ ሰውነታችንን ስለናንተ አሳልፈን እንሰጣለን አሏት ፤ እርሷም እግዚአብሔር አገራችንን በናንተ እጅ በጣላት ጊዜ ምሕረትን ቸርነትን እንድታደርጉልኝ ማሉልኝ አለቻቸው ፤

ወይቤልዋ እሙንቱ ዕደው ለእመ ኢያይዳእኪ በእንቲአነ ንገብር ምሕረተ ምስሌኪ ለእመ አግብአ እግዚአብሔር ለሀገርክሙ ለነ በጽድቅ ፤

ካሌብና ሰልሞንም አንች የኛን ምሥጢር አውጥተሽ ካልተገኘሽ እግዚአብሔርም በውነት አገራችሁን በእጃችን ከጣለልን እኛም ላንች ምሕረትን ቸርነትን እናደርጋለን አሏት ፤

፲፭፤ ወአውረደቶሙ በሐብል እንተ መስኮት እስመ ቤታ በጥቅም ውእቱ ወትነብር ይእቲ ውስተ ዓረፍት ፤

ቤቷ በቅጥር አጠገብ ነውና ከቅጽሩ ዛኒጋባ ጥላ እሷ ከዚያ ትኖር ነበርና በገመድ እየሠረች በመስኮት አወረደቻቸው ፤

፲፮፤ ወትቤሎሙ ሑሩ እንተ ደብር ከመ ኢይርከቡክሙ እለ ይዴግኑክሙ ወተኀብኡ ህየ ሠሉሰ መዋዕለ እስከ ይገብኡ እለ ይዴግኑክሙ ወእምዝ ትገብኡ ውስተ ፍኖትክሙ ፤

የሚከተሏችሁ ሰዎች እንዳያገኟችሁ ደጋ ደጋውን ሒዱ ፤ የሚከተሏችሁም ሰዎች እስኪመለሱ ድረስ ሦስት ቀን በዚያ ተሠወሩ ማለት እስከ ሦስት ቀን በጐዳና አትሒዱ ፤ ከሦስት ቀን በኋላ ግን በጐዳና ገብታችሁ ሒዱ አለቻቸው ፤ (ሐተታ) መከራ ትሰዳቸዋለች፣ አሕዛብ ውርጭ ይፈራሉና ደጋ ደጋውን ሒዱ እንጂ ቈላ ቈላውን አትሒዱ አሕዛብና ጕንዳን መንገድ (ጐዳና) አይለቁምና ዱር ዱሩን ሒዱ እንጂ በመንገድ ገብታችሁ አትሒዱ ፤ አሕዛብ በቀን እንጂ በሌሊት ቤታቸውን አይለቁ

ምና በሌሊት ሒዱ እንጂ በቀን አትሒዱ አለቻቸው ፤

፲፯፤ ወይቤልዋ እሙንቱ ዕደው ንጹሐን ንሕነ እመሐላኪ ዘአመሐልክነ ፣

እኛ ከዚህ ካማልሽን መሐላ ንጹሐን ነን አሏት ፤

፲፰፤ ናሁ ንሕነ ንበውእ ውስተ ጽንፈ ሀገር ወደዪ ዘንተ ፈትለ ቀይሐ ዘለይ ውስተ መስኮት እንተ ባቲ አውረድክነ ወአባኪኒ ወእመ ኪኒ ወአኃዊኪኒ አስተጋብኢ ኀቤኪ ውስተ ቤትኪ ፣

እነሆ እኛ ወደከተማው እንገባ ለን ፣ እኛን ባወረድሽበት መስ ኮት ይህንን ቀይ ሐር አዝግ ተሽ አባትሽንና እናትሽን ወን ድሞችሽንም ካንች ዘንድ በቤ ትሽ ሰብስበሽ ተቀመጭ ፤

፲፱፤ ወኵሉ ዘወፅአ አፍአ እምነ ኆኀተ ቤትኪ ይመውት ፣ ወንሕነሰ ንጹሐን ንሕነ እምዝንቱ መሐላ ዘአ መሐልክነ ፣

ከቤትሽ ደጃፍ ወጥቶ የተገኘ ሰው ሁሉ ይሞታል ፣ እኛም ከዚህ ካማልሽን መሐላ ንጹ ሐን ነን ማለት እንዲህ ሳታ ደርጊ ተገኝተሽ ካንቺ አንድ ሰው ቢሞት በእኛ ዕዳ አይ ሆንብንም ፤

ወባሕቱ ኵሉ ዘሀለወ ምስሌኪ ውስተ ቤትኪ ለእመ ሞተ ላዕሌነ ኃጢአት ፣

ነገር ግን ከብትሽን ሰውሽን ሁሉ ከቤትሽ ሰብስበሽ አኑረሽ አንድ ሰው ቢሞት ዕዳው በኛ ይሆናል ፤

፳፤ ወለእመሰ ከሠትኪ ነገረነ ንጹ ሐን ንሕነ እምዝንቱ መሐላኪ ፣

ነገር ግን ምሥጢራችንን ብታ ወጭ ከዚህ ከመሐላሽ ንጹሐን ነን ማለት ልታስገድይን ሰዎ ችሽን ልከሽ እግዚአብሔር ከሞት ቢያወጣን ከመሐላሽ ነፃ ነን ፤

፳፩፤ ወትቤሎሙ ይኩን በከመ ትቤሉ ወፈነዎቶሙ ወሖሩ ወአሠ ረት ዝክተ ፈትለ ዘለይ በመስኮት ፣

እሷም እናንተ እንዳላችሁት ይሁን ብላ ሸኝታ ሰደደቻቸው ፣ በመስኮቷም ያን ቀይ ሐር አዘ ጋችበት ፤ አንድም በመስኮቷ ቀይ ሐር ጋረደችበት ፤

፳፪፤ ወወፅኡ ወሖሩ ውስተ ደብር ወነበሩ ህየ ሠሉሰ መዋዕለ እስከ ገብኡ እለ ዴገንዎሙ ወኀሠሥዎሙ ወኢረከብዎሙ ውስተ ፍናዋት ፣

እነሱም ወጥተው ደጋ ደጋውን ሔዱ ፣ የተከተሏቸውም ሰዎች እስኪመለሱ ድረስ ሦስት ቀን ዱር ለዱር ሲሔዱ ሰነበቱ፣ በየ

ኀዳናውም ፈለጓቸው ፣ አላገኟ
ቸውም ፤

፳፫፤ ወገብኡ እልክቱ ዕደው ወወ
ረዱ እምደብር ወነለፉ ወበጽሑ
ኀበ ኢያሱ ወልደ ነዌ ወዜነውዎ
ኵሎ ዘገብሩ ፣

ሊሰልሉ ሔደው የነበሩት
ሰዎች ደጋ ደጋውን ሒደው
ተመልሰው መጡ ፣ የነዌ ልጅ
ኢያሱም ካለበት ደርሰው ያደ
ረጉትን ሁሉ ነገሩት ፤

፳፬፤ ወይቤልዎ አግብአ እግዚአብ
ሔር ኵሎ ምድረ ውስተ እዴነ
ወደንገፁ ኵሎሙ አሕዛብ እለ ይነ
ብሩ ውስተ ይእቲ ምድር እምኔነ ፣

እግዚአብሔር አገሩን ሁሉ
በጃችን ጣለልን (በእጃችን አሳ
ልፎ ሰጠን) በኢያሪኮ የሚ
ኖሩ ሰዎችም ሁሉ ከኛ የተ
ነሣ ደነገጡ አሉት ፡፡

## ምዕራፍ ፫

፩፤ ወጌሠ በጽባሕ ኢያሱ ወግዕዙ
እምሰጢን ወበጽሑ ዮርዳኖስ ውእቱ
ወኵሉ ደቂቀ እስራኤል ወነደሩ
ህየ እንበለ ይእድዉ ፣

ኢያሱ በነጋ ጊዜ ገሠገሠ ፣ የእ
ስራኤል ልጆች ሁሉና እሱ ከሰ
ጢን ተጉዘው ዮርዳኖስ ደረሱ ፣
ዮርዳኖስንም ሳይሻገሩ ከዚያው
አደሩ ፤

፪፤ ወእምድኅረ ሠሉስ መዋዕል በኡ
ጸሐፍት ማዕከለ ትዕይንት ፣

ከሦስት ቀንም በኋላ ሹማም
ንቱ ከሠፈሩ መካከል ገቡ ፤

፫፤ ወአስተነለፉ ለሕዝብ ወይቤል
ዎሙ እምከመ ርኢክሙ ታቦተ
ሕጉ ለእግዚአብሔር አምላክነ ፤
ወካህናተኒ ወሌዋውያነኒ ዘይጸው
ርዋ ገአዙ አንትሙኒ እምካህናቲ
ክሙ ወትልዉ ድኅሬሃ ፣

ከከተማውም ገብተው ለሕዝቡ
አዋጅ ነገሩ ፣ የፈጣሪያችን የእ
ግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦ
ትን ተሸክመው ካህናትና ሌዋ
ውያንን ካያችሁ በኋላ እናንተም
ከቦታችሁ ተነሥታችሁ እሷን
ተከትላችሁ ተጓዙ ፤

፬፤ ወባሕቱ ርኁቀ ይኩን ማዕከሌ
ክሙ ወማዕከሌሃ መጠነ እስራ ምእት
በእመት ወበመስፈርቱ ቁሙ ፣

ነገር ግን በናንተና በታቦተ
ጽዮን መካከል ሁለት ሽህ ክንድ
ያህል የራቀ ይሁን ፣ ሳትቀር
ቡም በመጠን ቁሙ ፤

ወኢትቅረብዋ ከመ ታእምሩ ውስተ
ፍኖት እንተ ተሐውሩ እስመ ኢሖ
ርክምዋ ለይእቲ ፍኖት ትካት ፣

ከቀድሞ ጀምሮ ይችን መንገድ
ሂዳችሁባት አታውቁምና የም
ትሔዱባትን መንገድ ታውቁ

ዘንድ ወደ ታቦተ ጽዮን አት
ቅረቡ ፤

፭፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለሕዝብ አን
ጽሑ ርእሰክሙ ለጌሠም እስመ
ጌሠመ ይገብር እግዚአብሔር መድ
ምመ ለክሙ ፤

ኢያሱ ሕዝቡን ነገ እግዚአብ
ሔር ለናንተ ድንቅ ነገር ያደ
ርጋልና ለነገ ራሳችሁን ንጹሕ
አድርጉ አላቸው ፤

፮፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለካህናት
ንሥኡ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
ወሑሩ ቅድመ ሕዝብ ወነሥኡ
ካህናት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር
ወሖሩ ቅድመ ሕዝብ ፤

ኢያሱ ካህናቱንም የእግዚአብ
ሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን
ይዛችሁ በሕዝቡ ፊት ተጓዙ
አላቸው ፤ ካህናቱም ታቦተ
ጽዮንን ይዘው በሕዝቡ ፊት
ተጓዙ ፤

፯፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ
ናሁ በዛቲ ዕለት እእኅዝ አዕቢከ
በቅድመ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል
ከመ ያእምሩ ከመ ሀሎኩ ምስሌከ
በከመ ሀሎኩ ምስለ ሙሴ ፤

እግዚአብሔር ኢያሱን ከሙሴ
ጋር በረድኤት እንደኖርኩ ካን
ተም ጋር በረድኤት እንድኖር
ያውቁ ዘንድ እነሆ በዚች ቀን
በእስራኤል ልጆች ፊት አከብ
ርሀ ዘንድ እጀምራለሁ ፤

፰፤ ወይእዜኒ አዝዞሙ ለካህናት እለ
ይፀውሩ ታቦተ ወበሎሙ እምከመ
ቦእክሙ ውስተ ጽንፈ ማዩ ለዮር
ዳኖስ ቁሙ ውስቴቱ ፤

አሁንም ታቦተ ጽዮንን የተሸ
ከሙ ካህናትን ወደ ዮርዳኖስ
ውሃ ዳርቻ በገባችሁ ጊዜ በው
ስጡ ቁሙ ብለህ እዘዛቸው ፤

፱፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ እስ
ራኤል ቅረቡ ዝየ ወስምዑ ቃለ እግ
ዚአብሔር አምላክነ ፤

ኢያሱ የእስራኤልን ልጆች ወደ
ዚህ ቀርባችሁ የፈጣሪያችን የእ
ግዚአብሔርን ቃል ስሙ አላ
ቸው ፤

፲፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ በዝንቱ ተአ
ምሩ ከመ ሕያው ውእቱ እግዚአ
ብሔር ዘምስሌክሙ ፤

ኢያሱም ከናንተ ጋራ በረድኤት
የሚኖር እግዚአብሔር ሕያው
እንደሆነ በዚህ ታውቃላችሁ
አላቸው ፤

ወአጥፍኦ ያጠፍኦሙ እምቅድመ ገጽ
ክሙ ለከናኔዎን ወለኬጤዎን ወለፌ
ርዜዎን ወለኤዌዎን ወለአሞሬዎን
ወለኢያቡሴዎን ወለጌርጌሴዎን ፤

እኒህን ሰባቱን ነገሥታተ አሕ
ዛብን ከፊታችሁ ፈጽሞ ያጠፋ
ቸዋል ፤

፲፩፡ ወናሁ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እግዚአ ኵሉ ምድር ተዓዱ ቅድሜክሙ ዮርዳኖስ ።

እነሆ ምድርን ሁሉ የፈጠረ የዓለም ሁሉ ጌታ የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትም ከናንተ አስቀድሞ ዮርዳኖስን ትሻገራለች ።

፲፪፡ ወኅረዩ ለክሙ ፲ተ ወ፪ተ ዕደወ እምደቂቀ እስራኤል ፩ደ ፩ደ ብእሴ እም፩ዱ ፩ዱ ነገድ ።

ከእስራኤል ልጆች ከያንዳንዱ ነገድ አንዳንድ ሰው አወጣጥ ታችሁ አሥራ ሁለት ሰው ምረጡ አላቸው ።

፲፫፡ ወሶበ ዓቀሙ እገሪሆሙ ካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ውስተ ማየ ዮርዳኖስ ይነጽፍ ማየ ዮርዳኖስ ። ወማይኒ ዘይወርድ እምላዕሉ ይቀውም ።

የእግዚአብሔርን የሕጉን ማደሪያ ታቦት የተሸከሙ ካህናት እግራቸውን በዮርዳኖስ ውሃ መካከል በአቆሙ ጊዜ የዮርዳኖስ ውሃ ይደርቃል፣ ከላይ ወደ ታች ይወርድ የነበረው ውሃም ይገታል አላቸው ።

፲፬፡ ወእምዝ ሶበ ግዕዙ ሕዝብ እማኅደሪሆሙ ከመ ይእድውዎ ለዮርዳኖስ ወካህናትኒ ያዑ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወሖሩ ቅድመ ሕዝብ ።

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ዮርዳኖስን ይሻገሩ ዘንድ ከሠፈራቸው በተጓዙ ጊዜ ካህናቱም የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ተሸክመው በሕዝቡ ፊት ተጓዙ ።

፲፭፡ ወሶበ ቦኡ ካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ውስተ ዮርዳኖስ ወተጠምቃ እገሪሆሙ ለካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕግ ውስተ ጽንፉ ለዮርዳኖስ ።

የእግዚአብሔርን የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የሚሸከሙ ካህናት ወደ ዮርዳኖስ በገቡ ጊዜ የካህናቱ እግራቸውም በዮርዳኖስ ውሃ በተነከረ ጊዜ ።

፲፮፡ ወቆመ ማይ ዘይወርድ እምላዕሉ ወቆመ ከመ ዓረፍት እንዘ ይርኅቅ ቀዊመ ጥቀ እስከ ደወለ ቀርያታርም ወዘይወርድ ወረደ ውስተ ባሕር ወእስከ ባሕረ ኤሎን ነጽፈ ወየብሰ ወቆሙ ሕዝብ አንጻረ ኢያሪኮ ።

ከላይ ወደታች የሚወርደው ውሃ እስከ ቀርያታርም አውራጃ ድረስ ርቆ እንደ ግድግዳ ቆመ፣ የሚወርደውም ወደባሕሩ ወርዶ እስከ ባሕረ ጨው ድረስ ፈጽሞ ደረቀ (ሸሸ) ሕዝቡም በኢያሪኮ አንጻር ቆመው ነበር ።

፲፯፤ ወካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ቆሙ ውስተ ይቡስ ማዕከለ ዮርዳኖስ ርሡያኒ ሆሙ ፤

የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የተሸከሙ ካህናትም ልብሰ ተክህኖውን ለብሰው ደረቅ ሁኖላቸው በዮርዳኖስ መካከል ቁመው ነበር ፤

ወኵሉ ደቂቀ እስራኤል አደዉ እንተ ማዕከለ የብስ እስከ ተገምሩ ኵሉ ሕዝብ ወአደዉ ዮርዳኖስ ፤

የእስራኤልም ልጆች ሁሉ ሕዝቡ ዮርዳኖስን አካተው እስኪሻገሩ ድረስ በደረቅ ዮርዳኖስን ተሻገሩ ፤ ለጊዜው እንዲህ ተደርጓል ለኋላው ምሳሌ ነው ፤ ኢያሱ የጌታ ፤ ውሃው የጥምቀት ፤ ካህናቱ የምእመናን ምሳሌ ናቸው ፡፡

## ምዕራፍ ፬

፩፤ ወሰበ ተገምሩ ኵሉ ሕዝብ ዓዲወ ዮርዳኖስ ይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ንሣእ ፲ተ ወ፪ተ ዕደወ ፩ደ ፩ደ ብእሴ እም፩ዱ ፩ዱ ነገድ ፤

ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ተካተው በተሻገሩ ጊዜ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው ከያንዳንዱ ነገድ አንዳንድ ሰው መርጠህ አሥራ ሁለት ሰው አምጣ አለው ፤

፪፤ ወአዝዞሙ ከመ ያንሥኡ ሎሙ እምዝየ እማዕከለ ዮርዳኖስ እምኀበ ቆሙ እገሪሆሙ ለካህናት ዓሠርተ ወክልኤተ አእባነ ከዋዋተ ፤

ቀሊላን ሲል ነው ፤ የካህናቱ እግር ከቆመበት ከዮርዳኖስ መካከል አሥራ ሁለት ሰዎች ቀለል ቀለል ያሉ አሥራ ሁለት ደንጊያዎች ይሸከሙ ዘንድ እዘዛቸው ፤

፫፤ ወንሥእዎን ምስሌክሙ ወዕቀብዎን በበነገድክሙ ኀበ ኀደርክሙ ሆየ በሌሊት ፤

ከናንተ ጋራም ይዛችኋቸው ተጓዙ ሌሊት በያደራችሁበት ቦታ በየነገዳችሁ ጠብቋቸው አላቸው ፤

፬፤ ወጸውዐ ኢያሱ ፲ተ ወ፪ተ ዕደወ እምክቡራኒሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፩ደ ፩ደ ብእሴ እም፩ዱ ፩ዱ ነገድ ፤

ኢያሱም ከእስራኤል ልጆች ከከበሩት ወገን የሚሆኑ ከያንዳንዱ ነገድ አንዳንድ ሰው መርጦ አሥራ ሁለት ሰዎችን ጠራ ፤

፭፤ ወይቤሎሙ ንዑ ወአምጽኡ ቅድሜየ ወቅድመ እግዚአብሔር እማዕከለ ዮርዳኖስ ወንሥኡ እም

ዝየ አሐተ አሐተ እብነ ወፁሩ ውስተ መታክፍቲክሙ በከመ ኍላቊሆሙ ለ፲ ወ፪ቱ ነገደ እስራኤል ፤

ኢያሱም ኑ ከዚህ ከዮርዳኖስ መካከል አሥራ ሁለት ደንጊያ ወደ እግዚአብሔርና ወደኔ ፊት አምጥታችሁ በአሥራ—ሁለቱ ነገደ እስራኤል ቍጥር በጫን ቃችሁ ተሸከሙ ፤

፮፤ ከመ ይኩናክሙ ተአምረ ወይን በራክሙ ለዝሉፉ ፤

ለዘላለሙ ምልክት ሁነው ይኖ ሩላችሁ ዘንድ ፤

ከመ ሶበ ተስእለከ ወልድከ ጌሠመ ወይቤለከ ምንት እላንቱ አእባን ፤

ልጅህም ነገ እነዚህ ድንጋዮች ምንድን ናቸው ብሎ በጠየቀህ ጊዜ ፤

፯፤ ንግሮ አንተ ለወልድከ ወበሎ እስመ ነጽፈ ዮርዳኖስ ተከዚ እምቅ ድመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ፤

ወንዙን ስንሻገር ዮርዳኖስ ከእ ግዚአብሔር ከሕጉ ማደሪያ ታቦት ፊት ሸሸች ፤ ደርቆ ነበ ርና የዚያ ምልክት ነው ብለህ አንተ ለልጅህ ንገረው ፤

ወይኩናክሙ እላንቱ አዕባን ተዝ ካረ ለክሙ ለደቂቀ እስራኤል እስከ ለዓለም ፤

እነዚህም ደንጊያዎች ለናንተ ለእስራኤል ልጆች እስከ ዘለዓ ለም መታሰቢያ ይሁኗችሁ አላ ቸው ፤

፰፤ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ ኢያሱ ወነሥኡ ፲ወ፪ተ አእባነ እማዕከለ ዮርዳኖስ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለኢያሱ ወሶበ ተገምሩ ዓዲወ ደቂቀ እስራ ኤል ፤

የእስራኤልም ልጆች ኢያሱ እን ዳዘዛቸው አደረጉ ጌታ ኢያሱን እንዳዘዘው ዮርዳኖስን ተካተው በተሻገሩ ጊዜ ከዮርዳኖስ መካ ከል አሥራ ሁለት ደንጊያ ተሸ ክመው አመጡ ፤

ወዐቀብዎን ምስሌሆሙ ውስተ ተዓ ይኒሆሙ ወሤምዎን በህየ ፤

በሠፈራቸው ከነሱ ጋር ጠብ ቀው አኖሯቸው ፤

፱፤ ወአቀመ በህየ ኢያሱ ካልዓተ አእባነ ፲ወ፪ተ ውስተ ዮርዳኖስ ውስተ ውእቱ መካን ኀበ ቆማ እገሪሆሙ ለካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕግ ፤ ወሀለዋ ህየ እስከ ዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት ፤

ኢያሱም የሕጉ ማደሪያ ታቦ ትን የተሸከሙ የካህናት እግ ሮች በቆሙበት በዮርዳኖስ መካ ከል ሌሎችን አሥራ ሁለት ደን ጊያዎች አቆመ ፤ እስከ ዛሬ ድረስም ከዚያ ይኖራሉ ፤ ሲጽፍ እስከ ዛቲ ዕለት አለ ፤ (ሐተታ) በዮርዳኖስ ዳርቻ ስድስቱን

ባንድ ወገን ፣ ስድስቱን ባንድ ወገን ተክሏቸዋል፣ ምሳሌ ነው፣ አሥራ ሁለቱ ሰዎች ያሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ፣ ደንጊያው የመከራቸው ፣ እነዚያ ደንጊያ ውን ተሸክመው እንደሔዱ ሐዋ ርያትም መከራ እየተቀበሉ ማለት እለ ቶማስ አቅማዳቸውን እየተሸከሙ አስተምረዋልና ፤

፲፤ ወቆሙ ካህናት እለ ይፀወሩ ታቦተ ሕግ ማዕከለ ዮርዳኖስ እስከ ፈጸመ ኢያሱ ኵሎ ዘአዘዞ እግዚ አብሔር ከመ ይንግሮሙ ለሕዝብ ወአፍጠኑ ዓዲወ ሕዝብ ፣

የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የተሸ ከሙ ካህናትም ኢያሱ እግዚአ ብሔር ያዘዘውን ሁሉ ለሕዝቡ ነግሮ እስኪጨርስ ድረስ በዮር ዳኖስ መካከል ቁመው ነበር ፣ ሕዝቡም ዮርዳኖስን ፈጥነው ተሻገሩ ፤

፲፩፤ ወሶበ ተገምሩ ዓዲወ ሕዝብ ዐደወት ታቦተ ሕግሂ ወእልክቱሂ አዕባን እለ ቅድሜሆሙ ፣

ሕዝቡም ዮርዳኖስን አካተው በተሻገሩ ጊዜ የሕጉ ማደሪያ ታቦትም ተሻገረች፣ በፊታቸው ያሉ እነዚያን ደንጊያዎችም ይዘዋቸው ተሻገሩ ፤

፲፪፤ ወዓደዉ ደቂቀ ሮቤል ወደቂቀ ጋድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ ርሡ ያኒሆሙ ቅድመ ደቂቀ እስራኤል በከመ አዘዞሙ ሙሴ ፣

የሮቤልና የጋድ ልጆች የምና ሴም ነገድ እኩሌታ ተጸርረው (ተሰልፈው) ሙሴ እንዳዘዛቸው በእስራኤል ልጆች ፊት ተሻ ገሩ ፤

፲፫፤ ፵፻ ቅኑታኒሆሙ ለቀትል ዐደዉ ቅድመ እግዚአብሔር ከመ ይትቃተልዋ ለኢያሪኮ ሀገር ፣

አራት ሽህ ሰዎች ለመዋጋት የጦር መሣሪያቸውን ታጥቀው ኢያሪኮን ይወጓት ዘንድ በእግ ዚአብሔር ፊት ተሻገሩ ፤

፲፬፤ ወበይእቲ ዕለት አዕበዮ እግዚ አብሔር ለኢያሱ በቅድመ ኵሉ ደቂቀ እስራኤል ወፈርህዎ ከመ ሙሴ አምጣነ ሕያው ውእቱ ፣

በዚያችም ቀን ጌታ ኢያሱን በእስራኤል ልጆች ፊት አከበ ረው አገነነው ፣ ሙሴን ባለ በዘ መኑ ሁሉ ይፈሩት እንደነበረ ፈሩት ፤ አንድም ሙሴን ይፈ ሩት እንደነበረ ኢያሱንም ባለ በዘመኑ ሁሉ ፈሩት ፤

፲፭፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢ ያሱ ፣

እግዚአብሔርም ኢያሱን እን ዲህ አለው ፤

፲፯፤ አዝዞሙ ለካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ከመ ይፃኡ እማዕከለ ዮርዳኖስ ።

የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የተሸከሙ ካህናትን ከዮርዳኖስ መካከል ይወጡ ዘንድ እዘዛቸው አለው ፤

፲፯፤ ወአዘዞሙ ኢያሱ ለካህናት ወይቤሎሙ ፃኡ እምዮርዳኖስ ።

ኢያሱም ካህናቱን ከዮርዳኖስ ውጡ ብሎ አዘዛቸው ፤

፲፰፤ ወኮነ ሶበ ወፅኡ ካህናት እለ ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እማዕከለ ዮርዳኖስ ወኬዱ በእገሪሆሙ ውስተ ምድር ።

የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን የተሸከሙ ካህናት ከዮርዳኖስ መካከል በወጡ ጊዜ እግሮቻቸውም የብስን በረገጡ ጊዜ ማለት ከወንዙ ወጥተው በየብስ በሔዱ ጊዜ እንዲህ ሆነ፤

ሮጸ ማየ ዮርዳኖስ ወገብአ ውስተ መካናቲሁ ወሖረ ከመ ትካት ወበጽሐ እስከ ድንጋጌሁ ።

ዮርዳኖስም ፈጥኖ ወደቦታው ተመለሰ እንደ ቀድሞውም ሔደ ከዳር እስከ ዳር መላ ፤

፲፱፤ ወእመ ፲ ለሠርቀ ቀዳሚ ወርኅ ወፅኡ ሕዝብ እምዮርዳኖስ ወግዕዙ ውስተ ገልገላ መንገለ ሠርቀ ፀሐይ እምኢያሪኮ ።

ሚያዝያ በባተ በአሥረኛው ቀን ሕዝቡ ከዮርዳኖስ ወጥተው ከኢያሪኮ በፀሐይ መውጫ በኩል ወዳለ ወደገልገላ ተጓዙ ፤

፳፤ ወዓቀሞን ኢያሱ ለእማንቱ አዕባን ፲ወ፪ቱ ውስተ ገልገላ ።

ኢያሱም እነዚያን አሥራ ሁለቱን ደንጊያዎች በገልገላ አቆማቸው ፤

፳፩፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ እስራኤል ሶበ ተስእሉክሙ ደቂቅ ክሙ ወይቤሉክሙ ምንት እላንቱ አዕባን ።

ኢያሱም የእስራኤልን ልጆች እንዲህ አላቸው ። ልጆቻችሁ እሊህ ደንጊያዎች ምንድን ናቸው ብለው በጠየቋችሁ ጊዜ ፤

፳፪፤ ዜንውዎሙ ለደቂቅክሙ ወበልዎሙ እስመ ከመ የብሰ ዐደውናሁ ለዝንቱ ዮርዳኖስ ።

ለልጆቻችሁ እንዲህ ብላችሁ ንገሯቸው ይህን ዮርዳኖስን በደረቅ ተሻግረነዋልና ስለዚህ ነው ብላችሁ ንገሯቸው አላቸው ፤

፳፫፤ እስመ አይበሳ እግዚአብሔር ለማየ ዮርዳኖስ ቅድሜነ እስከ ነዓዱ ።

እኛ እስክንሻገር እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ውሃ ከፊታችን ስላ ደረቃት ፤

በከመ ገብራ እግዚአብሔር ለባሕረ
ኤርትራ እንተ አይበሳ እግዚአብ
ሔር አምላክነ እምቅድሜነ እስከ
ኅለፍነ ፤

እስክንሻገራት ድረስ ፈጣሪያ
ችን እግዚአብሔር ከፊታችን
ያደረቃት የኤርትራን ባሕር
ከዚህ ቀድሞ እንዳደረጋት
ማለት ከ፫ት ከ፬ት እንደከፈ
ላት የዮርዳኖስንም ውሃ ከፊ
ታችን ስላደረቃት ፤

፳፬፤ ከመ ያእምሩ ኵሉ አሕዛበ
ምድር ከመ ጽኑዕ ውእቱ ኃይሉ
ለእግዚአብሔር ወከመ ትፍርህዎ
አንትሙኒ ለእግዚአብሔር አምላ
ክነ በኵሉ ግብሩ ፤

በምድር ያሉ አሕዛብ ሁሉ የእ
ግዚአብሔር ኃይሉ ጽኑ እንደ
ሆነ ያውቁ ዘንድ ፤ እናንተም
ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን በሥ
ራው ሁሉ ትፈሩት ዘንድ ::

## ምዕራፍ ፭

፩፤ ወእምዝ ሶበ ሰምዑ ኵሉ ነገ
ሥተ አሞሬዎን እለ ሀለዉ ማዕዶተ
ዮርዳኖስ መንገለ ባሕር ወኵሉ ነገ
ሥተ ፊንቂስ እለ ሀለዉ መንገለ
ባሕር ከመ አይበሳ እግዚአብሔር
ለተከዜ ዮርዳኖስ እምቅድመ ገጸሙ
ለደቂቀ እስራኤል ፤

ከዚህ በኋላ በባሕር አንፃር
በዮርዳኖስ ማዶ የሚኖሩ የአ
ሞሬዎን ነገሥታትና በባሕር
አጠገብ (አንፃር) የሚኖሩ የፊ
ንቂስ ነገሥታት እግዚአብሔር
የዮርዳኖስን ወንዝ ከእስራኤል
ፊት እንዳደረቃት (እንደከፈ
ላት) በሰሙ ጊዜ ፤

ተመስወ ልቦሙ ወተጠሰየ ወነጥኡ
ዘይሄልዩ እምቅድመ ገጸሙ ለደ
ቂቀ እስራኤል ፤

ልቡናቸው እንደሰም ቀልጦ
ጠፋ ፤ ከእስራኤልም ልጆች ፊት
አስበው የሚናገሩትን አጡ ፤

፪፤ ወእምድኅረ እማንቱ መዋዕል
ይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ግበር
ለከ መጣብሐ ዘእብን እምእብነ
እዝኅ ወንበር ወግዝሮሙ ለደቂቀ
እስራኤል ፤

ከነዚያ ወራቶች በኋላ እግዚ
አብሔር ኢያሱን ከቡልጭት
ደንጊያ ወገን የደንጊያ ሻፎ
(ምላጭ) አብጅ ፤ ተቀምጠህም
የእስራኤልን ልጆች ግረዛቸው
አለው ፤

፫፤ ወገብረ ሎቱ ኢያሱ ኵሎ
መጣብሐ ዘእብነ እዝኅ ወገዘሮሙ
ለደቂቀ እስራኤል በውስተ መካን
ዘስሙ ወግረ ቍልፈት ፤

ኢያሱም ከቡልጭት ደንጊያ
ወገን ምላጭ አበጅቶ ስሙ ብል
ታቸውን የተገረዙበት በሚባል
ቦታ የእስራኤልን ልጆች ገረ
ዛቸው ፤

፬፤ ወበበይነ ዝንቱ ገዘሮሙ ኢያሱ
ለኵሉ ሕዝብ እለ ወፅኡ እምግ
ብጽ ኵሉ ተባዕቶሙ ወኵሉ ሕዝብ
ዕደው መስተቃትላን እለ ሞቱ በገ
ዳም በፍኖት ወሂአሙ እምግብፅ ኮኑ
ግዙራን ፤

ስለዚህ ነገር ኢያሱ ከግብፅ
የወጡ ሕዝቡን ወንድ ወንዱን
ሁሉ ገረዛቸው ፣ ከግብፅ ወጥ
ተው በምድረ በዳ የሞቱት
አርበኞች ሰዎች ሁሉ ተገርዘው
ነበርና ፤

፭፤ ወኵሉ ሕዝብ እለ ተወልዱ በፍ
ኖት በገዳም ወሂአሙ እምድረ
ግብፅ እስመ እሙንቱ ኢኮኑ ግዙ
ራን ፣

ነገር ግን ከግብፅ ምድር ከወጡ
በኋላ በምድረ በዳ በጎዳና የተ
ወለዱት ሕዝቡ ሁሉ አልተገረ
ዙም ነበርና ፤

፮፤ እስመ ፵ ዓመተ ያዱ እስራኤል
ውስተ ገዳም ዘመድበራ እስከ ተፈ
ጸሙ ኵሉ ሕዝብ መስተቃትላን
እለ ወፅኡ እምድረ ግብፅ እለ ክሕዱ
ትእዛዘ እግዚአብሔር ፣

ወደ ምድረ ርስት ትገባላችሁ
ቢላቸው አንገባም ብለው የእግ
ዚአብሔርን ትእዛዝ ያፈረሱ
አርበኞች ሰዎች ሁሉ ፈጽመው
እስከ ጠፉ ድረስ እስራኤል
መድበራ በሚባል ምድረ በዳ
አርባ ዘመን ስለዞሩ አልተገረ
ዙም ነበርና ፤

ወይቤሎሙ እግዚአብሔር ከመ ኢይ
ርአይዋ ለይእቲ ምድር ዘመሐለ
እግዚአብሔር ለአበዊነ ከመ የሀ
በነ ምድረ እንተ ትውኅዝ ሐሊበ
ወመዓረ ፣

ተድላ ደስታ የሚገኝባት አገር
ከነዓንን ያወርሰን ዘንድ ለአባቶ
ቻችን የማለላቸው ያችን አገር
እንዳያይዋት እግዚአብሔር ነግ
ሯቸዋልና ፤

፯፤ ወህየንተ ዚአሆሙ ዓቀመ ውሉ
ዶሙ ዘገዘሮሙ ኢያሱ እስመ ኢኮኑ
ግዙራነ እስመ በፍኖት ተወልዱ
ወኢተገዝሩ ፣

በመንገድ ተወልደው አልተገ
ረዙም ነበርና ኢያሱ የገረዛ
ቸው ልጆቻቸውን ስለነሱ ፈንታ
ተካ ፤

፰፤ ወአመ ተገዝሩ ነበሩ ትዕይንተ
ወወዓሉ እስከ የሐይዉ ፣

እነዚህም በተገረዙ ጊዜ እስኪ
ድኑ ድረስ ሠራዊቱ ሠፈር አድ
ርገው ዋሉ እንጂ አልተጓዙም ፤
(ሐተታ) ስለምን በደንጊያ ገረ
ዛቸው ቢሉ እናንተ ጽኑዓነ ልብ
ናችሁ ወደ እኔ ብትመለሱ በጽኑ
ሥልጣኔ የልቡናችሁን ጽናት
(ክፋት) አርቅላችኋለሁ ሲል
ጌታ በደንጊያ እንዲገረዙ አደ
ረገ ፤

፱፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ
ናሁ ዮም በዛቲ ዕለት አውፃእኩ
ትዕይርቶሙ ለግብፅ እምኔክሙ ወሰ

መየ ስሞ ለውእቱ መካን ገልገላ እስከ ዮም ወእስከ ዛቲ ዕለት ፤

እነሆ ዛሬ በዚች ቀን ግብፃው ያን የሚሰድቧችሁን ስድብ አራ ቅሁላችሁ ፤ በምድረ በዳ የተ ወለዱት ልጆች ሳይገረዙ ቢቀሩ እስራኤል ቆላፋን በተባሉ ነበ ርና የዚያንም ቦታ ስሙን እስከ ዛሬ ድረስ ገልገላ አለው ፤ የእስ ራኤል ቀኋልፈታቸው የራቀበት ቦታ ማለት ነው ፤ ሲጽፍ እስከ ዛቲ ዕለት ይላል ፤

፲፡ ወነደሩ ደቂቀ እስራኤል ውስተ ገልገላ ወገብሩ ፋሲካ አመ ፲ወ፬ ለሠርቀ ቀዳሚ ወርኅ በሠርከ በዓ ረቢሃ ለኢያሪኮ በማዕዶተ ዮርዳኖስ በውስተ ገዳም ፤

የእስራኤል ልጆች በገልገላ ሠፍ ረው አደሩ ፤ መጀመሪያ ወር የሚሆን ሚያዝያ በባተ ባስራ አራተኛው ቀን በኢያሪኮ በም ዕራቧ በኩል በዮርዳኖስ ማዶ በምድረ በዳ በሠርክ ፋሲካን አደረጉ ፤

፲፩፡ ወበልዑ እምእክለ ምድር ናዕተ ሐዲሰ ፤

ከዚያች አገር እህል አዲሱን እህል ቂጣ አድርገው በሉ ፤ (የፈ ንቆንን እህል ዘርፈው በሉ) ፤

፲፪፡ ወበይእቲ ዕለት ኀልቀ መና በሳኒታ እምዘበልዑ እክለ ምድር ወኢረከቡ እንከ መና ደቂቀ እስራ ኤል ዳግመ እስመ አረሩ ብሔረ ፊንቆን በውእቱ ዓመት ፤

የዚያን አገር እህል ከበሉ በኋላ በማግስቱ በዚያች ቀን መናው ቀረ ፤ በዚያ ወራት የፊንቆንን አዝመራ ዘርፈው በልተዋልና የእስራኤል ልጆች ዳግመኛ መናውን አላገኙም ፤

፲፫፡ ወኮነ እንዘ ሀለወ ኢያሱ ውስተ ኢያሪኮ ነጸረ በአዕይንቲሁ ወርእየ ብእሴ ይቀውም ቅድሜሁ ወሰይፍ ምሉሕ ውስተ እዴሁ ፤

ኢያሱ በኢያሪኮ ሳለ እንዲህ ሆነ ፤ በእጁ የተመዘዘ ሰይፍ የያዘ አንድ ሰው በፊቱ ቁሞ በዓይኑ አየ ፤ ኮነ ያለውን ነጸረ ብሎ ተረጎመው ፤ በሰው አም ሳል ስለታየው ብእሲ አለው እንጂ መልአክ ነው ፤

ወቀርበ ኢያሱ ወይቤሎ እምስብእ ዚአነ አንተ አው እምፀርነ ፤

ኢያሱም ቀርቦ አንተ ከኛ ሰዎች ወገን ነህን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህ ? አለው ፤

፲፬፡ ወይቤሎ አንሰ መልአከ ኃይሉ ለእግዚአብሔር ወይእዜ በጻሕኩ ፤

እኔስ እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጥበት መልአክ ነኝ ፤ አንድም የሠራዊት መላእክት አለቃ ነኝ አሁንም ልረዳህ ወደ አንተ መጥቻለሁ አለው ፤

፲፭፤ ወወድቀ ኢያሱ በገጹ ወሰገደ ሎቱ ውስተ ምድር ወይቤሎ ምንት አቀመከ ኀበ ገብርከ ፤

ኢያሱም በግንባሩ ከመሬት ወድቆ ሰገደለት ፤ ከእኔ ከባሪያህ ዘንድ ምን አቁሞሃል አለው ፤

፲፮፤ ወይቤሎ መልአከ ኃይሉ ለእግዚአብሔር ለኢያሱ ፍታሕ አሣእኒከ እምእገሪከ እስመ መካን ኀበ ትቀውም ምድር ቅድስት ይእቲ ወገብረ ኢያሱ ከማሁ ፤

እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጥበት መልአክም ኢያሱን የምትቆምባት ምድር የከበረች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው ፤ ኢያሱም መልአኩ እንዳዘዘው አደረገ ፤ (ሐተታ) ስንኳን ከሰማያዊ መልአክ ሲገናኙ ከምድራዊ ንጉሥ ሲገናኙ በትሕትና መቅረብ ይገባልና ፤ አንድም የምትሔድባት ኢያሪኮ የጸናች ናትና አሣዕነ ፍርሃትን ከእግረ ልቡናህ አርቅ ሲለው ነው ።

## ምዕራፍ ፮

፩፤ ወኢያሪኮሰ ዕፁት ይእቲ ወጥቅም ላዕሌሃ ፤

ኢያሪኮ ግን በብረት መዝጊያ የተዘጋች ናት ቅፅርም ነበራት ፤ አንድም ቅፅርት ይእቲ ይላል ፤ ሰባት ቅፅር ያላት ናት ፤ አንድም እጉት ይእቲ በጦር የተከበበች ናት ቅትልት ይእቲ ይላል በጦር የተወጋች ናት ፤

ወአልቦ ዘይወጽእ እምውስቴታ ወአልቦ ዘይበውእ ኀቤሃ ፤

ከእሷ የሚወጣ ወደ እሷም የሚገባ አልነበረም ፤

፪፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ናሁ አገብእ ለኢያሪኮ ውስተ እደዊከሙ ወለንጉሣ ዘውስቴታ ወእለ ጽኑዓን እሙንቱ ወኃያላን ፤

እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው፤ እነሆ ኢያሪኮን በእጃችሁ እጥላታለሁ ፤ በውስጧ ያለ ንጉሡንም አርበኞቹንም ሁሉ በእጃችሁ እጥላቸዋለሁ አለው ፤

፫፤ ወአንተሰ አቅሞሙ ላዕሌሃ ውስተ ዓውዳ ለኵሎሙ መስተቃትላን ወይዑድዋ ለሀገር ኵሎሙ ዕደው መስተቃትላን ውስተ ዓውዳ ለይእቲ ሀገር በበምዕር ወከማሁ ግበሩ ሰዱሰ መዋዕለ ፤

አንተ ግን በኢያሪኮ በዙሪያዋ አርበኞችን ሁሉ አቁማቸው ኃያላኑ ሰዎችም ሁሉ ያችን አገር አንድ አንድ ጊዜ ይዙሯት ስድስት ቀንም እንዲህ አድርጉ ፤

፬፤ ወሰብአቱ ካህናት ይንሥኡ ፯ተ አቅርንተ ዘኢዮቤል ቅድመ ታቦት ወአመ ሳብዕት ዕለት ሳብዓ ይዑ

ድዋ ለሀገር ወይንፍሑ ካህናት በአ ሙንቱ አቅርንት ፣

ሰባት ካህናት በታቦት ፊት በኢዮቤልዩ በዓል የሚነፉ ሰባ ቱን ቀንደ መለከት ይያዙ፣ በሰ ባተኛው ቀን ግን አገሪቱን ሰባት ጊዜ ዙረው ካህናቱ ቀንደ መለ ከቱን ይንፉ ፤

፭፤ ወሶበ ነፍሑ በአሙንቱ አቅር ንት ዘኢዮቤል እምከመ ሰማዕክሙ ቃለ ቀርን ለይወውዑ ኵሎሙ ሕዝ ዛብ ኅቡረ ፣

የኢዮቤልን በዓል ሲያከብሩ የሚመቱትን ሰባቱን ቀንደ መለ ከት በነፉ ጊዜ ፣ ነጋሪቱንም በመቱ ጊዜ ፣ የመለከቱን የነጋ ሪቱን ድምፅ ከሰማችሁ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ በአንድነት ይደ ንፉ ፤

ወእምከመ ወውዑ እሙንቱ ይወ ድቅ ለሊሁ ዓረፋቲሃ ለሀገር ታሕ ቴሆሙ ወይባእ እንከ ኵሉ ሕዝብ ወይሩጽ ፩ዱ ፩ዱ ቅድመ ገጹ ውስተ ሀገር ፣

ሕዝቡ ከደነፉ በኋላ (ከአገረሩ በኋላ) የኢያሪኮ ቅጽሯ እየተ ናደ ከበታቻቸው ይወድቃል ፣ ከዚያ በኋላ አንዱም አንዱ ፈጥኖ ወደ ኢያሪኮ ይግባ አለው ፤

፮፤ ወጸውዖሙ ኢያሱ ለካህናት ወይቤሎሙ ንሥኡ ታቦተ ሕግ ወ፯ቱ ካህናት ይንሥኡ ፯ተ መጣ ቅዕተ ዘኢዮቤል በቅድመ እግዚአ ብሔር ፣

ኢያሱም ካህናቱን ጠርቶ የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ተሸከሙ ፣ ሰባቱ ካህናትም በኢዮቤልዩ በዓል የሚነፉ ሰባቱን ቀንደ መለ ከት በእግዚአብሔር ፊት ይያዙ አላቸው ፤

፯፤ ወይቤሎሙ አዝዝዎሙ ለሕዝብ ከመ ይሑሩ ወይዑድዋ ለሀገር መስ ተቃትላንሂ ይሑሩ ምስለ ንዋየ ሐቅ ሎሙ ቅድመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአ ብሔር ፣

ሕዝቡም ሒደው ኢያሪኮን ይዞ ሯት ዘንድ እዘዟቸው ፣ አርበ ኞችም ጋሻ ጦራቸውን ይዘው የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ በሆነች ታቦት ፊት ይሒዱ አላቸው ፤

፰፤ ወነሥኡ ፯ቱ ካህናት ፯ተ መጣ ቅዕተ ቅዱሳነ በከመ ይቤሎሙ ኢያሱ ከመ ይሑሩ ቅድመ እግዚ አብሔር ወሐዊሮሙ ይጥቅዑ በኃ ይል ወበትእምርት ወታቦተ ሕጉሂ ለእግዚአብሔር ትተልዎሙ ፣

ሰባቱ ካህናትም በእግዚአብሔር ፊት ይሔዱ ዘንድ ኢያሱ እንደ ነገራቸው ልዩ የሆኑ ሰባቱን ቀንደ መለከት ይዘው ሔዱ ፣ ሒደውም ምልክት ባለው ዓመታት አበርትተው ይንፉ (ይምቱ)፣ የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦት ትከተላቸዋለች ፣

፱፤ ወመስተቃትላንሰ ፍጽመ የሐውሩ ፣ ወካህናትሂ ይጠቅዑ በመጣቅዕት ወእለሂ ይትኬወሉ ድኅረ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር የሐውሩ እንዘ ይነፍሑ ቀርነ ፣

አርበኞች ጋሻ ጦራቸውን ይዘው በፊት በፊት ይሔዱ ነበር ፣ ካህናቱም ነጋሪቱን ይመቱ ነበር ፣ የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ በሆነች ታቦት በኋላ የሚከተሉትም ቀንደ መለከቱን እየነፉ ይሔዱ ነበር ፤

፲፤ ወአዘዞሙ ኢያሱ ለሕዝብ ከመ ኢይውክቱ ወአልቦ ዘይሰምዕ ቃሎሙ መኑሂ ከመ ኢይፃእ ቃል እምአፉሆሙ እስከ አመ ውእቱ ይኤዝዞሙ ከመ ይወውዑ ፣

ኢያሱም ሕዝቡን ግር ግር እንዳይሉ ፣ ከአፋቸው (ከአንደበታቸው) ቃል እንዳይወጣ ፣ የድንፋታ ቃል ያሰሙ ዘንድ እሱ እስኪያዛቸው ድረስ ማንም ማን ቃላቸው የሚሰማ እንዳይኖር አዘዛቸው ፤

፲፩፤ ወሖረት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወያደታ ለሀገር ፣ ወእምዝ ገብአት ውስተ ትዕይንት ወቤተት ሀየ ፣

የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትም ከካህናቱ ጋር ሒዳ ኢያሪኮን ዞረቻት ፣ ከዚህ በኋላ ወደ እስራኤል ሠፈር ተመልሳ በዚያ አደረች ፤

፲፪፤ ወበሳኒታ ዕለት ተንሥአ ኢያሱ በጽባሕ ወካህናትኒ ፆሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ፣

በማግሥቱ ኢያሱ ማልዶ ተነሣ፣ ካህናቱም የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ተሸከመው ተነሡ ፤

፲፫፤ ወ፯ቱ ካህናት ነሥኡ ፯ተ መጣቅዕተ ቅዱሳነ ወሖሩ ቅድመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ወይተልዉ መስተቃትላን ፣

ሰባቱ ካህናትም ልዩ የሆነ ፯ ቀንደ መለከት ይዘው በእግዚአብሔር በሕጉ ማደሪያ ታቦት ፊት ሔዱ ፣ ዐርበኞችም እነሱን ተከትለው ሔዱ ፤

ወእምዝ ይተልዉ እለ ተርፉ ሕዝብ ወየሐውሩ ድኅረ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እንዘ ይነፍሑ በአቅርንት ወካህናትሂ ይጠቅዑ በመጣቅዕት ፣

ከዚህ በኋላ የቀሩት ሕዝቡ ቀንደ መለከቱን እየነፉ በእግዚአብሔር በሕጉ ማደሪያ ከታቦቱ በኋላ ይሔዱ ነበር ካህናቱም ነጋሪት ይመቱ ነበር ፤

፲፬፤ ወከሎ ሕዝብ ዘተርፉ ዖድዋ ለሀገር ፩ደ ጊዜ አመ ሳኒታ ዕለት እንዘ ይቀርብዋ ወእምዝ ካዕበ ገብኡ ውስተ ትዕይንት ወከመዝ ገብሩ ስዱሰ መዋዕለ ፣

የቀሩት ሕዝቡም ሁሉ በማግስቱ ቀርበው ኢያሪኮን አንድ

ጊዜ ዞሯት ከዚያ በኋላ ዳግ
መኛ ወደሠፈራቸው ተመለሱ
እንዲህ እያደረጉ ስድስት ቀን
ዞሯት ፤ (ሐተታ) አንድ ጊዜ
ዙረው እንደ ፊት አቦ ፣
አንድ ጊዜ ዙረው እንደ ደብረ
ምጥማቅ ፣ አንድ ጊዜ ዙረው
እንደ አባ ብርሌ ፣ አንድ ጊዜ
ዙረው እንደ ደብረ ብርሃን ፣
አንድ ጊዜ ዙረው እንደ ቅዱስ
ገብርኤል ፣ አንድ ጊዜ ዙረው
እንደ አጠናቅር፣ እንዲህ እያሉ
፮ ቀን ዙረዋል ፣ በ፯ኛው ቀን
፯ ጊዜ ዙረው ዋካታ ድንፋታ
አደረጉ፣ ቅጽሩ እየተናደ ወደቀ፣
እስራኤል በዚች እየገቡ አሕዛ
ብን አጥፍተዋል፣ ምሳሌ ነው ፣
ኢያሱ የጌታ ፣ ኢያሪኮ የምእ
መናን ፣ አሕዛብ የአጋንንት ፣
ኢያሱ አሕዛብን አጥፍቶ ኢያ
ሪኮን እጅ እንደአደረገ ጌታም
አጋንንትን ድል ነሥቶ በምእ
መናን አድሮ ለመኖሩ ምሳሌ፣
አንድም ሰልሞን የጌታ፣ ራኬብ
የምእመናን ፣ ራኬብ ከአሕዛብ
ብዙ ወንድ ስታገባ ስታወጣ
ኑራ ባንድ በሰልሞን እንደተወ
ሰነች አሕዛብም ልዩ ልዩ ጣዖ
ታትን ሲያመልኩ ኑረው በአ
ንድ በጌታ አምነው ለመኖራ
ቸው ፣ ሁለቱ ገብኞች የሁለቱ
ሕገጋት ፣ ከራኬብ ደጃፍ የቀ
መው ዓላማ የመስቀል ፣ ሐሩ
የሥጋው የደሙ ፣ መስኮቱ የከ
ናፍረ ምእመናን ምሳሌ ነው ፤

፲፭፤ ወኮነ አመ ሣብዕት ዕለት ተን
ሥኡ ጊዜ ይገውህ ጽባሕ ወዖድዋ
ለሀገር ከማሁ ስብዓ ወዳዕሙ በይ
እቲ ዕለት ዖድዋ ስብዓ ለሀገር ፣

በ፯ኛው ቀን እንዲህ ሆነ፣ (በነጋ
ጊዜ) ጎሕ በቀደደ ጊዜ ተነሥ
ተው አገሪቱን ፯ ጊዜ ዞሯት ፣
በዚያች ቀን ብቻ ኢያሪኮን ፯
ጊዜ ዞሯት ፤

፲፮፤ ወኮነ ሶበ ዖድዋ ስብዓ ለሀገር
ጠቅዑ ካህናት በመጣቅዕቲሆሙ
ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ እስራ
ኤል ወውዑ እስመ አግብአ እግዚ
አብሔር ለነ ፣

ከተማዪቱን ፯ ፯ ጊዜ በዞሯት
ጊዜ እንዲህ ሆነ፣ ካህናቱ ነጋሪ
ታቸውን ይመቱ ቀንደ መለከ
ታቸውን ይነፉ ጀመረ ፣ ኢያ
ሱም የእስራኤልን ልጆች እግዚ
አብሔር ሀገሪቱን በእጃችን ጥሎ
ልናልና አግሩ ደንፉ አላቸው ፤

፲፯፤ ወአህረምናሃ ለዛቲ ሀገር
ወኵሉ ዘውስቴታ ይኩን ለእግዚ
አብሔር ጸባኦት ዘእንበለ ረዓብ ዘማ
እንተ ታሐይዉ ኪያሃ ወኵሎ ዘሀ
ለወ ውስተ ቤታ እስመ ኀብአቶሙ
ለሰብእ ዓይን እለ ፈነውን ፣

ያችን ሀገር ሥርዓተ ሞት ሠራ
ንባት ፤ አንድም ከሕይወት

በሞት ከደስታ በመከራ እርም
አደረግናት ፣ እሷን ከምታድ
ኗት ከረዓብ ዘማና በቤቷ ካለው
ሰው ሁሉ በቀር በኢያሪኮ የተ
ገኘው ገንዘብ ሁሉ ለአሸናፊ
እግዚአብሔር ይሁን ፣ የላክናቸ
ውን ጉበኞች በቤቷ ሠውራ
አድናቸዋለችና ከረዓብ ዘማ
በቀር ፤

፲፰፤ ወአንትሙ ባሕቱ ዑቁ ወኢት
ንሥኡ እምዘ ሕሩም ዘአሕረምነ
ወኢትፍትዉ ወኢትንሥኡ እም
ኔሁ ፣

ነገር ግን እናንተ ከዚህ ከተ
ከለከለው ገንዘብ እንዳታነሡ
እወቁ ፣ ከዚህም ከተከለከለው
ገንዘብ ወዳችሁ አታንሡ ፤

ወእመ አኮሰ ትገብርዋ ርግምተ ለት
ዕይንት ወትቀጠቅጡነ ፣

ከተከለከለው ገንዘብ ወዳችሁ
ብታነሡ ግን ይህችን ወገን የተ
ረገመች ታደርጓታላችሁ ፣ እኛ
ንም ታጠፉናላችሁ ፤

፲፱፤ ወኵሉ ወርቅ ወብሩር ወብ
ርት ወሐፂን ቅዱስ ይኩን ለእግዚ
አብሔር ወውስተ መዝገቡ ይባእ ፣

በኢያሪኮ የተገኘ ወርቅ ብር
ብረት ሁሉ ለእግዚአብሔር የተ
ለየ ይሁን ፣ ወደ እግዚአብሔር
ዕቃ ቤትም ይግባ ፤

፳፤ ወወውዑ ሕዝብ ወካህናትኒ
ጠቅዑ በመጣቅዕቲሆሙ ወኀቡረ
ወውዑ ሕዝብ በዓቢይ ውውዓ ወጽ
ኑዕ ፣

ሕዝቡ አወኩ ደነፉ ፣ ካህናቱም
ነጋሪታቸውን መቱ ቀንደ መለ
ከታቸውን ነፉ ፣ ሕዝቡም ቃላ
ቸውን አሰምተው በአንድነት
አወኩ ደነፉ ፤

ወወድቀ ኵሉ ዓረፋቲሃ ዘዓውዳ
ወቦኡ ኵሉ ሕዝብ ውስተ ሀገር
ወኵሎሙ ርቱዐ ውስተ ሀገር ቅድ
ሜሆሙ ወረከብዋ ለሀገር ፣

በዙሪያዋ ያለ ቅጽሯ እየተናደ
ወደቀ ፣ እስራኤል ሁሉ ወደፊ
ታቸው እየሮጡ (ፈጥነው) ወደ
ኢያሪኮ ገቡ ፣ ሀገሪቱንም እጅ
አደረጓት ፤

፳፩፤ ወአሕረማ ኢያሱ እምተባእት
እስከ አንስት እምንኡሶሙ እስከ
ልሂቆሙ ወእስከ ላሕም ወበግዕ
ወእስከ አድግ ቀተሉ በሐፂን ፣

ኢያሱ በዚያች ሀገር ሥርዓተ
ሞት ሠራባት ፤ አንድም ከተ
ድላ ደስታ በመከራ እርም አደ
ረጓት ፣ በውስጧ ያለውን ሁሉ
ከወንድ እስከ ሴት ፣ ከታናና
ሾቹ እስከ ታላላቆቹ ከላም ከበግ
እስከ አህያ ድረስ በጦር አጠፉ ፤

፳፪፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለእልክቱ
፪ቱ ወራዙት ሰብአ ዓይን እለ ርእ
ይዋ ለብሔር ሑሩ ወባኡ ውስተ

ቤታ ለእንታክቲ ብእሲት ዘማ ወእ ውፅእዋ እምህየ ወኵሎ ዘሀለወ ምስሌሃ በከመ መሐልክሙ ላቲ ።

ኢያሱም ኢያሪኮን ሰልለው የመጡ ሁለቱን ጉበኞች ከዚያች ከአዳነቻችሁ ሴት ቤት ሔዳችሁ ከዚያ አውጧት እንደ ማላችሁላት ከእርሷ ጋር ያለውንም ሁሉ አውጡ አላቸው ፤

፳፫፤ ወቦኡ እልክቱ ፪ቱ ወራዙት ሰብአ ዓይን እለ ርእይዋ ለይእቲ ሀገር ውስተ ቤተ ረዓብ ዘማ ወእ ውፅእዋ ።

ሁለቱ ጉበኞች ካሌብና ሰልሞንም ረዓብ ዘማ ወዳለችበት ቤት ገብተው ወደውጭ አወጧት ፤

ወለአቡሃ ወለእማ ወለአኃዊሃ ወለ ኵሉ ዘመዳ ወኵሎ ዘባቲ ወአብጽሕዋ እስከ አፍአ ውስተ ትዕይንቶሙ ለእስራኤል ።

አባትና እናቷን ፣ ወንድሞቿንና ዘመዶቿን፣ ያላትን ገንዘብ ሁሉ ከኢያሪኮ አውጥተው ከእስራኤል ሠፈር አደረሷት ፤ አንድም ከኢያሪኮ ውጭ እስከ እስራኤል ሠፈር አደረሷት ፤ አንድም ከእስራኤል ሠፈር እስከ ውጭ ድረስ ሸኟት ፤

፳፬፤ ወውዕየት ሀገር ምስለ ኵሉ ዘውስቴታ በእሳት ዘእንበለ ወርቅ ወብሩር ወኵሉ ብርት ወሐፂን ዘአብኡ ውስተ መዛግብተ ቤተ እግዚአብሔር ።

ወደ እግዚአብሔር ዕቃ ቤት ካገቡት ከወርቁ ፣ ከብሩ ፣ ከናሱና ከብረቱ በቀር ከተማይቱ በውስጧ ካለው ሁሉ ጋር በእሳት ተቃጠለች ፤

፳፭፤ ወረዓብ ዘማ ወኵሉ ቤተ አቡሃ አሕየወ ኢያሱ ነበረት ውስተ እስራኤል እስከ ዛቲ ዕለት ።

ረዓብ ዘማ ኢያሱ ካዳናቸው ካባቷ ወገኖች ሁሉ ጋር እስከ ዚች ቀን ድረስ በእስራኤል መካከል ተቀመጠች ፤

እስመ ኅብዓቶሙ ለሰብአ ዓይን እለ ፈነወ ኢያሱ ከመ ይርአይዋ ለሀገረ ኢያሪኮ ።

ኢያሪኮን ይኅበኟት ዘንድ ኢያሱ የላካቸውን ጉበኞች ከሰገነት ሠውራ አድናቸዋለችና ፤

፳፮፤ ወአምሐለ ኢያሱ በይእቲ ዕለት ወይቤ ርጉመ ለይኩን ዘያንሥአ ለዛቲ ሀገር በበኵሩ ለይሣርራ ወበደኃሪ ወልዱ ለያቅም ኆኅተ አንቀጸ ።

ኢያሱም በዚያች ቀን ይችን አገር አቀናለሁ የሚል ሰው የተረገመ ይሁን፣ በበኵር ልጁ ይመሥርታት ማለት መሠረቷን ሲጀምር የበኽር ልጁ ይሙት ፣ መቃን መድረኳን ሲያቆም ታናሹ ልጁ ይሙት አለ ፤

፳፯፣ ወሀለወ እግዚአብሔር ምስለ
ኢያሱ ወበጽሐ ስሙ ውስተ ኵሉ
ምድር ፤

እግዚአብሔርም ከኢያሱ ጋር
በረድኤት ነበረ ፤ ስሙም በእ
ስራኤል አገር ሁሉ ተነገረ ፤
ይህም የኢያሱ ቃለ መርገም
አልቀረም ፤ በአክዓብ ጊዜ ተደ
ርጓል ፤ አክዓብ ይህን የኢያሱን
ቃል አፍርሶ ያችን አገር ሲመ
ሠርት የበኵር ልጁ ሙቷል ፤
መቃን መድረኳን ሲያቆም
ታናሹ ልጁ ሙቷልና ወሣረራ
ለኢያሪኮ በአቤሮን በኵሩ ወአ
ቀመ ኆኅያቲሃ በዜጉብ ወልዱ
ዘይንእስ እንዲል ።

## ምዕራፍ ፯

፩፣ ወአበሱ ደቂቀ እስራኤል ዓቢየ
አበሳ ወነሥአ አካን ወልደ ከርሚ
ወልደ ዘንበሪ ወልደ ዛራ ዘእምነገደ
ይሁዳ እምዘአሕረሙ ወተምዐ እግ
ዚአብሔር ፤

ከይሁዳ ወገን የተወለደ የዛራ
ልጅ የሚሆን የዘንበሪ ልጅ
የከርሚ ልጅ አካን ለእግዚአ
ብሔር ካሳዩት ገንዘብ ሰርቆ
ወስዷልና የእስራኤል ልጆች
ጽኑ በደል በደሉ ፤ እግዚአብ
ሔርም በእስራኤል ልጆች ፈረ
ደባቸው ፤

፪፣ ወፈነወ ኢያሱ ዕደወ ውስተ ጋይ
እምኢያሪኮ እንተ መንገለ አዊን
መንገለ ጽባሒሃ ለቤቴል ፤

ኢያሱም የቤቴል ምሥራቅ በም
ትሆን በአዊን አጠገብ ካለች
ከኢያሪኮ ወደ ጋይ የሚጉበኙ
ሰዎችን ሰደደ ፤

ወይቤሎሙ ዕርጉ ወረአይዋ ለጋይ
ወዐርጉ እሙንቱ ዕደው ወርእይዋ
ለጋይ ፤

ከኢያሪኮ ወጥታችሁ ጋይን እዩ
ዋት አላቸው ፤ እነዚያም ሰዎች
ወጥተው ጋይን ጉበኟት ፤

፫፣ ወገብኡ ኀበ ኢያሱ ወይቤልዎ
ኢይዕርግ ኵሉ ሕዝብ አላ ፳፻አው
፴፻ ዕደው ይዕርጉ ወይትቃተልዋ
ለይእቲ ሀገር ወኵሉሰ ሕዝበ እግ
ዚአብሔር ኢትሰድ ሀየ እስመ ውኁ
ዳን እሙንቱ ፤

ጉበኞችም ወደ ኢያሱ ተመል
ሰው እንዲህ አሉት፤ ሁለት ሺህ
ወይም ሦስት ሺህ ሰዎች ወጥ
ተው ይችን አገር ይውጓት
እንጂ ሕዝቡ ሁሉ አይውጡ ፤
እነዚያ ጥቂቶች ናቸውና የእግ
ዚአብሔር ወገኖች እስራኤልን
ሁሉ ወደዚያ ወደጋይ አትው
ሰድ አሉት ፤

፬፣ ወዐርጉ እምሕዝብ ዘየአክሉ ፴፻
ወአገትዎሙ ሰብአ ጋይ ወጐዩ እም
ቅድመ ገጾሙ ፤

ከእስራኤል ወገን ፫ ሺህ ያህል
ወደ ጋይ ወጡ ፤ የጋይ ሰዎች

ድል አድርገው አበረሯቸው ፣ እስራኤል ከጋይ ሰዎች ፊት ሸሹ ።

፭፤ ወቀተሉ እምኔሆሙ በውስተ ጋይ ፴ወ፮ተ ዕደወ ወእምዝ ዴገንዎሙ እምኅበ አንቀጽ እስከ አጥፍእዎሙ ወቀተልዎሙ በውስተ ሙራድ ወደንገፀ ልቦሙ ለሕዝብ ወኮነ ከመ ማይ ፣

የጋይ ሰዎች ከእስራኤል ሠላሳ ስድስት ሰዎችን ገደሉ ፣ ከዚያም በኋላ እስኪያጠፏቸው ድረስ ከአደባባዩ በር ጀምሮ እየ ተከተሉ በቍልቍለቱ ገደሏቸው፣ የእስራኤልም ልቡና ደንግጦ እንደ ውሃ ቀዘቀዘ ።

፮፤ ወሠጠጠ አልባሲሁ ወወድቀ በገጹ ውስተ ምድር ቅድመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር እስከ ሠርክ ውእቱ ወሊቃውንቲሆሙ ለእስራኤል ወወደዩ መሬተ ውስተ ርእሶሙ ፣

ኢያሱም ልብሱን ቀደደ፣ በእግዚአብሔር ማደሪያ በታቦተ ጽዮን ፊት እሱ ከእስራኤል አለቆች ጋር እስከ ማታ ድረስ በግንባሩ ወድቆ ዋለ ፣ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ ።

፯፤ ወይቤ ኢያሱ ገነይኩ ለከ እግዚኦ እግዚእየ ለምንት አዕድዎ አዕደዎሙ ገብርከ ለእሉ ሕዝብ እምዮርዳኖስ ፣

ኢያሱም እንዲህ አለ ፣ አቤቱ ጌታዬ እኔ ላንተ እገዛለሁ፣ እኔ ባሪያህ ወገኖችህ እስራኤልን ከዮርዳኖስ እንዳሻግራቸው ለምን አዘዝኸኝ ።

ከመ ታግብኦሙ ውስተ እዴሆሙ ለአሞሬዎን ወከመ ያጥፍዑነ ሶበ ኀደርነ ወነበርነ ማዕዶተ ዮርዳኖስ ፣

በአሕዛብ እጅ ትጥላቸው ዘንድ፣ በዮርዳኖስ ማዶ ባደርን ጊዜም ያልፉን ዘንድ ዮርዳኖስን ለምን አሻገርኋቸው ፤ አንድም እንዲህ ከሆነስ በዮርዳኖስ ማዶ ብንኖር በተሻለን ነበር ።

፰፤ እግዚኦ ምንተ እንከ እብል ናሁ ሜጠ እስራኤል ዘባኖ ኀበ ፀሩ ፣

አቤቱ እነሆ እስራኤል ጀርባውን መልሶ ፣ አንገቱን ቀልሶ ከጠላቶቹ ሸሸ እንግዲህ ምን እላለሁ ።

፱፤ ወእምከመ ሰምዑ ከነዓን ወኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ዛቲ ምድር የዐግቱነ ወያጠፍዑነ እምድር ወምንተ ትሬሲ ለስምከ ዓቢይ ፣

የከነዓን ሰዎችና በዚች አገር የሚኖሩት ሁሉ ጥፋታችንን ከሰሙ ከወደኋላችን ከበው ከሀገራችን ያጠፉናል ፣ ገናና የሆነ ስምህ ሊመሰገንበት ምን ታደርጋለህ ፣ (ምንት ትረሲ) ምን ታደርግ አለ ።

፲፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ተንሥእ ወለምንት ትወድቅ አንተ በገጽከ ፣

እግዚአብሔር ኢያሱን ከወደቅ ህበት ተነሣ ፣ የበደሉ እስራኤል ናቸው ፣ አንተ በግንባርህ ለምን ትወድቃለህ አለው ፤

፲፩፤ አበሱ ሕዝብ ወክሕዱ ኪዳንየ ዘተካየድኩ ምስሌሆሙ ወነሥኡ እም ዘጎሩም ወሰረቁ ወወደዩ ውስተ ንዋ ያቲሆሙ ፣

ሕዝቡ በደሉ ፣ ከእነሱ ጋር የቃ ማማልኩትን መሐላየን አፍ ርሰው እርም ካሉት ገንዘብ ማለት ፣ ለነሱ ከተከለከለው ገንዘብ ሰርቀው ወስደው ከገን ዘባቸው ጋር ጨምረው ሠው ረውታል ፤

፲፪፤ ወኢይክሉ እንከ ደቂቀ እስራ ኤል ቀዊመ ቅድመ ፀሮሙ እስመ ርጉማን ኮኑ ፣

የተረገሙ ሁነዋልና ማለት በሕግ ከእኔ ተለይተዋልና እን ግዲህ ወዲህ የእስራኤል ልጆች ጀርባቸውን መልሰው፣ አንገታ ቸውን ቀልሰው ይሸሻሉ እንጂ በጠላቶቻቸው ፊት ቁመው መዋጋት አይችሉም ፤

ወኢይደግም እንከ ሀልዎ ምስሌ ክሙ ለእመ ኢያውፃእክሙ እምኔ ክሙ ዘርጉም ፣

ርጉም የሆነውን ሰው ዘጎሩም ቢል የተከለከለውን ገንዘብ ሰርቆ የወሰደውን ሰው ከናንተ ለይ ታችሁ ካላወጣችሁ እንግዲህ ወዲህ እኔም ከናንተ ጋር በረ ድኤት አልኖርም ፤

፲፫፤ ተንሥእ ወቀድሶሙ ወበሎሙ አንጽሑ ርእሰክሙ ለጌሠም ፣

ከዚህ ከወደቅህበት ተነሥተህ ሕዝቡን ለያቸው ፣ ለነገ ራሳች ሁን ከኃጢአት ንጹሕ አድርጉ በላቸው ፤

እስመ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘጎሩም ሀለወ ውስቴትክሙ ወኢትክሉ እንከ ቀዊመ ቅድመ ፀርክሙ እስከ ታሴስሉ እም ኔክሙ ዘጎሩም ፣

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብ ሔር፣ ለእግዚአብሔር የተለየ ውን ገንዘብ ሰርቆ የወሰደ ሰው ከናንተ ውስጥ አለና ያን ሰው ከናንተ ለይታችሁ በሞት እስክ ታርቁት ድረስ እንግዲህ ወዲህ በጠላቶቻችሁ ፊት መቆም አይ ቻላችሁም ብሏልና ፤

፲፬፤ ወይጊሡ በጽባሕ ወይትጋብኡ ኵሎሙ በበሕዘቢሆሙ ወሕዝብ ዘአርአየ እግዚአብሔር ሳዕሌሁ ለይ ትፋለጡ በበነገዶሙ፡ ወይቁሙ ፣

ማልደው ሒደው ሁሉም በየወ ገናቸው ይሰብሰቡ እግዚአብሔር በላያቸው ምልክት ያሰየባቸው ወገኖች ተለይተው በየወገናቸው ይቁሙ ፤

ወነገድ ዘአርአየ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ለይትፌለጡ ወይቁሙ በበቤቶሙ ወቤት ዘአርአየ እግዚአብሔር ላዕሌሁ ለይትፌለጡ ወይቁሙ በበብእሲሁ ፤

እግዚአብሔር በላያቸው ምልክት ያሳየባቸው ወገኖች አንዱም አንዱም ተለይተው ይቁሙ ፤

፲፭፤ ወብእሲ ዘአርአየ እግዚአብሔር በላዕሌሁ ለያውዕይዎ በእሳት ሎቱ ወለኵሉ ዘዚአሁ ፤

እግዚአብሔር በላዩ ምልክት ያሳየበትን ሰው እሱን ከወገኖቹ ከገንዘቡም ሁሉ ጋር በእሳት ያቃጥሉት ፤

እስመ ክሕደ ኪዳኖ ለእግዚአብሔር ወገብረ ኃጢአተ ላዕለ እስራኤል ፤

የእግዚአብሔርን መሐላ (ትእዛዝ) አፍርሷልና በእስራኤልም ላይ ኃጢአት ሠርቷልና ፤

፲፮፤ ወጌሠ ኢያሱ ወአስተጋብአሙ ለሕዝብ በበሕዘቢሆሙ ወአስተርአየ ላዕለ ሕዝበ ይሁዳ ፤

ኢያሱም ገሥግሦ ሒዶ ሕዝቡን በየወገናቸው ሰበሰባቸው፤ በይሁዳ ወገኖች ላይ ምልክት ታየ ፤

፲፯፤ ወተፈልጡ ሕዝበ ይሁዳ በበነገዶሙ ወአስተርአየ ላዕለ ነገደ ዛራ በቤቱ ወአስተርአየ ላዕለ ቤተ ዘንበሪ ፤

ነገደ ይሁዳም በየወገናቸው ተለዩ በነገደ ዛራ ላይ ምልክት ታየ ፤ ነገደ ዛራም በየወገናቸው ተለዩ ፤ ምልክቱ በዘንበሪ ወገኖች ላይ ታየ ፤

፲፰፤ ወተፈልጠ ቤተ ዘንበሪ በበብእሲሁ ወአስተርአየ ላዕለ አካን ወልደ ከርሚ ወልደ ዘንበሪ ወልደ ዛራ ዘእምሕዝበ ይሁዳ ፤

የዘንበሪ ወገንም አንዱም አንዱ ሰው ተለየ ፤ ከነገደ ይሁዳ የተወለደ የዛራ ልጅ የዘንበሪ የልጅ ልጅ በሚሆን በአካን ወልደ ከርሚ ምልክቱ ጎልቶ ታየ ፤ (ሐተታ) ምልክቱስ ምንድን ነው ቢሉ ሊቀ ካህናቱ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ይቆማል ፤ እስራኤል በየወገናቸው ሲያልፉ ያን ጊዜ ልብሰ ተክህኖው እቀደድ እቀደድ ይላል ፤ አንድም ይጠቁራል ድምፅ ያሰማል ፤

፲፱፤ ወይቤሎ ኢያሱ ለአካን ወልድየ አእኩቶ ለእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ወእመና ወአይድአኒ ምንተ ገበርከ ወኢትንባእ እምኔየ ፤

ኢያሱም አካንን የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔርን አመስግነው አለው ፤ አእኩቶ ያለውን

እመኖ ብሎ ደገመው ፤ አን ድም አመስግነው ፣ ወእመኖ አሌ አትበለው ምን አድርገሃል እስኪ ያደረግኸውን ንገረኝ ከእኔ ምንም ምን አትሠውር አለው ፤

፳፤ ወአውሥአ አካን ለኢያሱ ወይ ቤሎ አማን አነ አበስኩ ቅድመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ከመዝ ወከመዝ ገበርኩ ፣

አካን ለኢያሱ መለሰለት ፣ እን ዲህ አለው ፣ እኔ በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ፊት በውነት በድያለሁ እንዲህም እንዲህም አድርጌአለሁ ፤

፳፩፤ ወሶበ ርኢኩ በውስተ በርበር ፩ደ ልብሰ ወ፪ተ ምዕተ ጠፋልሐ ብሩር ወልሳን አሐቲ እንተ ወርቅ ተአክል ፶ ዲድርክመ ወተውላጣ ፈተውኩ ወነሣእኩ ፣

በዘረፋ ጊዜ ፬ ጎብር ፣ ፩ኛ ወርቀ ዘቦ የሆነች ፩ ልብስ ፣ ፪ መቶ ምዝምዝ ብር ፶ ወቄት የምትሆን አንዲት ልሳነ ወርቅ ባገኘሁ ጊዜ ለውሟን እሰጣለሁ ብዬ ወሰጃለሁ ፤

ወናሁ ሀለወ ድፉን ውስተ ደብተ ራየ ወጠፋልሐ ብሩርኒ ሀለወ መት ሕቴሁ ፣

እነሆ በድንኳኔ ውስጥ ቀብሬ አኑሬዋለሁ ምዝምዙም ብር በበታቹ ተቀብሮ ይገኛል አለው ፤

፳፪፤ ወፈነወ ኢያሱ ደቆ ወሮፁ ኀበ ትዕይንት ውስተ ደብተራሁ ወሀለወ ዝኩ ድፉን ውስተ ደብተ ራሁ ወብሩርኒ ሀለወ ምስሌሁ መት ሕቶ ፣

ኢያሱም የተቀበረውን ገንዘብ ለማስመጣት ብላቴኖቹን ላከ ፣ እነሱም ወደ ድንኳኑ ፈጥነው ሔዱ ፣ የተሰረቀው ገንዘብ በድ ንኳኑ ውስጥ ተቀብሮ ነበር ፣ ብሩም በበታቹ ተቀብሮ ተገኘ ፤

፳፫፤ ወአውፅኡ እምውስተ ደብተ ራሁ ወወሰዱ ኀበ ኢያሱ ወኀበ ኵሉ ሊቃናተ እስራኤል ወአንበሩ ቅድመ እግዚአብሔር ፣

እነዚያም መልእክተኞቹ ያን ገንዘብ ከተቀበረበት አውጥተው ወደ ኢያሱና ወደ እስራኤል አለቆች ሁሉ ወስደው በእግዚ አብሔር ፊት አኖሩት ፤

፳፬፤ ወነሥአ ኢያሱ ለአካን ወልደ ዛራ ወለውእቱ ብሩር ወለውእቱ ልብስ ወለይእቲ ልሳን እንተ ወርቅ ፣

ኢያሱም የዛራ ልጅ አካንን ከዚያ ብርና ልብስ ከዚያችም ወርቅ ጋር ይዞ ፤

ወወሰዱሙ ውስተ ቈላተ አኮር ለአ ካን ወለደቂቁ ወለአዋልዲሁ ወለአ ልሕምቲሁ ወለአባግዒሁ ወለአእዱ

ጊሁ ወለደብተራሁ ወለኵሉ ንዋዩ
ወወደዮሙ ውስተ ኤሜቃኮር ፤

አካንን ወንዶችና ሴቶች ልጆ
ቹን ፤ ላሞቹንም ፤ በጎቹንም ፤
አህዮቹንም ፤ ድንኳኑንና ገንዘ
ቡን ሁሉ ወስዶ በኤሜቃኮር
ጣላቸው ፤ ኤሜቃኮር መካነ
ሥራዌ መካነ ድምሳሴ ማለት
ነው ፤

፳፭፤ ወይቤሎ ኢያሱ ለአካን ለም
ንት ሠሮከነ ለይሥሩከ እግዚአብ
ሔር በከመ ዮም ወወገርዎሙ በእ
ብን ኵሎሙ እስራኤል ወአውዓይ
ዎሙ በእሳት ፤

ኢያሱ አካንን የማይገባ ሥራ
ሠርተህ ለምን አጠፋኸን ? አሁ
ንም እግዚአብሔር አንተን ያጥ
ፋህ አለው ፤ እስራኤልም ሁሉ
ልጆቹንም እሱንም በድንጋይ
ወግረው (መትተው) በእሳት
አቃጥለው ገደሏቸው ፤

፳፮፤ ወአቀሙ ላዕሌሁ ሐውልተ
ዕብን እስከ ዛቲ ዕለት ወኀደገ እግ
ዚአብሔር መቅሠፍተ መዓቱ ፤

እስከዚች ቀን ድረስ በላዩ ላይ
የደንጊያ ሐውልት አቆመበት ፤
እግዚአብሔርም ፈርዶ ያመጣ
ውን መቅሠፍት ተወ (ይቅር
አለ) ፤

ወበበይነ ዝንቱ ሰመዮ ኤሜቃኮር
እስከ ዛቲ ዕለት ፤

ስለዚህም ነገር እስከዚች ቀን
ድረስ የዚያን ቦታ ስሙን ኤሜ
ቃኮር አለው ፤ መካነ ሥራዌ
መካነ ድምሳሴ ማለት ነው ።

## ምዕራፍ ፰

፩፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ
ኢትፍራህ ወኢትደንግፅ ንሥአሙ
ምስሌከ ለኵሎሙ ዕደው መስተቃ
ትላን ወተንሥእ ወዕርግ ውስተ
ጋይ ፤

እግዚአብሔርም ኢያሱን እን
ዲህ አለው ፤ አትፍራ አትደ
ንግጥ ተነሥተህ አርበኞቹን
ሰዎች ሁሉ ካንተ ጋር ወደ ጋይ
ይዘኻቸው ውጣ ፤

እስመ ናሁ አግባእክዎ ውስተ እዴከ
ለንጉሠ ጋይ ወለሕዝቡሂ ወለሀገሩሂ
ወለምድሩሂ ፤

እነሆ የጋይን ንጉሥ ከሠራዊቱ
ከሀገሩ ከምድሩ ጋር በጅህ ጥዩ
ዋለሁና ፤

፪፤ ወትገብራ ለጋይ ወለንጉሣ በከመ
ገበርካ ለኢያሪኮ ወለንጉሣ ፤

ኢያሪኮን ከንጉሧ ጋር እንደ
አጠፋህ ጋይንም ከንጉሧ ጋር
ታጠፋለህ ፤

ወበርበረ እንስሳ በርብሩ ለርእስክሙ
ወባሕቱ ፊኑ ይዕግትዋ ለሀገር እንተ
መንገለ ከዋላሃ ፤

የከብቱንም የበጉንም ምርኮ
ለራሳችሁ ዘርፋችሁ ውሰዱ ፤
ነገር ግን ጋይን ከወደኋላዋ ይከ
ቧት ዘንድ ጦር ስደድ ፤ አንድም

በስተኋላዋ ከበው ያጠፏት ዘንድ ድብቅ ጦር አስቀምጥ አለው ፤

፫፤ ወተንሥአ ኢያሱ ወኵሉ ሕዝብ መስተቃትላን ወዐርጉ ውስተ ጋይ ወኀረየ ኢያሱ ፫ተ እልፈ ዕደወ ጽኑዓነ ወመስተቃትላነ ወኃያላነ ወፈነዎሙ በሌሊት ፤

ኢያሱም ከአርበኞች ወገኖቹ ሁሉ ጋር ተነሥቶ ወደ ጋይ ወጡ ኢያሱም ሦስት እልፍ ወይም ሠላሳ ሺሕ አርበኞች ሰዎችን መርጦ በሌሊት ላካቸው ፤

፬፤ ወአዘዞሙ ወይቤሎሙ ሑሩ ዘከመ ተአምሩ ዕግትዋ ለሀገር እንተ መንገለ ከዋላሃ ወኢትርኀቁ በሕቁ እምሀገር ወንበሩ ኵልክሙ ድልዋነ ክሙ ፤

እንደምታውቁት ሒዱችሁ አገሪቱን ከወደኋላዋ ክበቧት ፤ ከሷም ፈጽማችሁ አትራቁ ፤ ሁላችሁም ለጦር የተዘጋጃችሁ ሁናችሁ ተቀመጡ ብሎ አዘዛቸው ፤

፭፤ ወአንሰ ወኵሉ ሕዝብ ዘምስሌየ ንቀርብ ኀበ ሀገር ወሶበ ወፅኡ ሰብአ ጋይ ወተቀበሉነ ከመ ቀዲሙ ንጐይይ እምቅድመ ገጾሙ ፤

እኔና ከኔ ጋር ያሉ ወገኖቼም ወደ ከተማው እንቀርባለን ፤ የጋይ ሰዎች በጦርነት ወጥተው በተቀበሉን ጊዜ ግን እንደ ቀድሞው ከፊታቸው እንሸሻለን ፤

፮፤ ወሶበ ወፅኡ ወዴገኑነ ናርኅቆሙ እምሀገር ወይብሉ ነትዑ እሉሂ እምቅድመ ገጽነ ከመ ቀዲሙ ወንሕነሂ ንጐይይ እምቅድመ ገጾሙ ፤

ወጥተው በተከተሉንም ጊዜ የሸሽን እየመሰልን ከከተማው እናርቃቸዋለን ፤ እነዚህም እንደ ቀድሞው ከፊታችን ሸሹ እያሉ ይከተሉናል ፤ እኛም ከፊታቸው እንሸሻለን ፤

፯፤ ወእምዝ እንከ ተንሥኡ አንትሙሂ ወአኀዝዋ ለሀገርሙ ወያገብአ እግዚአብሔር አምላክክሙ ውስተ እዴክሙ ፤

ከዚህ በኋላ እናንተ ተነሡታችሁ አገራቸውን ያዟት ፤ እጅ አድርጓት ፤ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ጋይን በእጃችሁ ይጥላታልና ፤

፰፤ ወእምከመ በእክምዋ ለሀገሮሙ አውዕይዋ በእሳት ወግበሩ በከመ እቤለክሙ ናሁ አዘዝኩክሙ ፤

ወደ ከተማቸውም በገባችሁ ጊዜ ከተማዪቱን በእሳት አቃጥሏት ፤ እነሆ አቃጥሏት ብዬ አዝዣችኋለሁና እንደነገርኋችሁ አድርጉ ፤ አንድም እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርጉ አላቸው ፤

፱፤ ወፈነዎሙ ኢያሱ ወሖሩ ይዕግ ትዋ ለሀገር ወነበሩ ማዕከለ ቤቴል ወማዕከለ ጋይ እምባሕረ ጋይ ወቤተ ኢያሱ ሀየ በይእቲ ሌሊት ማዕከለ ሕዝብ ።

ኢያሱም ላካቸው ፤ እነሱም ከተ ማዪቱን ይከቧት ዘንድ ሒደው በጋይና በቤቴል መካከል በጋይ በስተምዕራቧ በኩል ተቀመጡ ፤ ኢያሱም በዚያች ሌሊት በሕ ዝቡ መካከል አደረ ፤

፲፤ ወጌሠ በጽባሕ ወርእዮሙ ለሕ ዝብ ወዐርጉ ውእቱ ወሊቃውንቲ ሆሙ ለእስራኤል ፍጽመ ቅድመ ሕዝብ ላዕለ ጋይ ።

ማልዶ ገሥግሦ ሒዶ ሕዝቡን አያቸው ፤ እሱና የእስራኤል አለቆች አስቀድሞ በሠራዊቱ ፊት ወደ ጋይ ወጡ ፤

፲፩፤ ወዐርጉ ኵሎሙ ሕዝብ መስ ተቃትላን ምስሌሁ ወበጽሑ ወቀርቡ ቅድመ ሀገር እንተ መንገለ ጽባሒሃ ወዓአት ማዕከሎሙ ወማዕከለ ጋይ ፤

አርበኞች ሰዎች ሁሉ ከሱ ጋር ወጡ ፤ በምሥራቋ በኩል በከተ ማዪቱ ፊት ለፊት ቀረቡ ፤ በጋ ይና እስራኤል በተሰበሰቡበት መካከል ዱር ነበር ፤

፲፪፤ ወነሥአ ኢያሱ ፶፻ተ ብእሴ ወአንበሮሙ ይዕግቱ ማዕከለ ቤቴል ወማዕከለ ጋይ መንገለ ባሕረ ጋይ ፤

ኢያሱ አምስት ሺ ሰዎች መርጦ በጋይና በቤቴል መካከል ይከቡ ዘንድ በጋይ በስተምዕራቧ በኩል አኖራቸው ፤

፲፫፤ ወአንበሩ ኵሉ ሕዝብ ተአይኒ ሆሙ እንተ መንገለ መስዑ ለሀገር ወጽንፋ እስከ ባሕረ ሀገር ወሖረ ኢያሱ በይእቲ ዕለት ማዕከለ ውእቱ ዒአት ፤

ሕዝቡ ሁሉ ሠራዊቶቻቸውን በጋይ በመስዕ በኩል በሰሜን በኩል አኖሩ ፤ ዳርቻዋም እስከ ሀገሩ ምዕራብ ድረስ ነው ፤ ኢያሱም በዚያች ቀን በዱሩ መካከል ሔደ ፤

፲፬፤ ወሶበ ሰምዐ ንጉሠ ጋይ ጌሠ ፍጡነ ወወፅኡ ሰብአ ሀገር ወተቀበ ልዎሙ እንተ ቅድሜሆሙ ከመ ይትቃተልዎሙ ውእቱ ወኵሉ ሕዝብ ዘምስሌሁ በጊዜሃ መንጸረ ዓረባ ፤

የጋይ ንጉሥም በሰማ ጊዜ ፈጥኖ ገሥግሦ ሔደ ፤ እሱና ከእሱ ጋር ያሉ ሠራዊቱም ሁሉ በጊዜዋ ጊዜ በምዕራቧ በኩል ይወጓቸው ዘንድ ወጥተው ፊት ለፊት ተቀበሏቸው ፤

ወኢያእመረ ውእቱሰ ከመ አኀት ዎሙ እንተ መንገለ ከዋላሃ ለሀገር ፤

እሱ ግን የጋይ ንጉሥ ከተማ ዪቱን በስተኋላዋ የኢያሱ አር በኞች እንደከበቧት አላወቀም ነበር ፤

፲፭፡ ወሶበ በጽሕዎሙ ጐየ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል እምቅድመ ገጸሙ ወነትዑ ውስተ ፍኖተ ገዳም ፤

የጋይ ሰዎች በደረሱባቸው ጊዜ ኢያሱና እስራኤል ሁሉ የፈሩ መስለው ወደ ምድረ በዳው መንገድ ፈጽመው ሸሹ ፤

፲፮፡ ወዔሉ ኵሉ ሕዝበ ብሔር ወተለውዎሙ ወሰደድዎሙ ወዴገንዎሙ እምድኅሬሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ፤

ባገር ያሉ ሰዎች ሁሉ እልል እያሉ በኋላቸው እየተከተሉ አባረሯቸው ፤

፲፯፡ ወርኀቀሙ እሙንቱ እምሀገር አልቦ ዘተርፈ ወኢመኑሂ ውስተ ጋይ ወውስተ ቤቴል ዘኢተለዎሙ ወዘኢዴገኖሙ ለእስራኤል ወኀደግዋ ለሀገር ርኅውታ ፤

እነዚያ ከሀገር በራቁ ጊዜ እስራኤልን ያልተከተላቸው በቤቴልና በጋይ ማንም ማን አልነበረም ከተማዪቱንም እንደተከፈተች ትተዋት ወጡ ፤

፲፰፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ አልዕል እዴከ በጋይሶ ዘውስተ እዴከ ላዕለ ጋይ እስመ ውስተ እዴከ አግባእክዋ ፤

እግዚአብሔር ኢያሱን ጋይን በእጅህ ጥያታለሁና በእጅህ በያዝከው ጋሻ ወደ ጋይ ጥቀሳቸው ፤

ወእለሂ ፀገቱ ለይትነሥኡ ፍጡነ እምካህናቲሆሙ ወአልዓለ ኢያሱ በጋይሶ ላዕለ ሀገር ፤

በኋላ ከበው የተቀመጡትም ሰዎች ሁሉ ከተቀመጡበት ቦታ ፈጥነው ይነሡ አለው፤ ኢያሱም እጁን ከፍ አድርጎ በያዘው ጋሻ ጠቀሳቸው ፤

፲፱፡ ወእለሂ ፀገቱ ተንሥኡ ፍጡነ እመካናቲሆሙ ወሮጹ ሶበ አልዓለ እዴሁ በጋይሶ ወቦኡ ሀገረ ወአኀዝዋ ወአውዓይዋ ፍጡነ በእሳት ፤

በእጁ በያዘው ጋሻ በጠቀሳቸው ጊዜ የከበቡት ሰዎች ከቦታቸው ፈጥነው ተነሥተው ወጡ ፤ ወደ ከተማዪቱም ገብተው እጅ አደረጓት ፤ ፈጥነውም በእሳት አቃጠሏት ፤

፳፡ ወሶበ ነጸሩ ድኅሬሆሙ ሰብአ ጋይ ወርእዩ ጢሰ የዐርግ ውስተ ሰማይ እምውስተ ሀገሮሙ ኃጥኡ እንከ ኀበ ይጐይዩ ኢለፌ ወኢለፌ ወሕዝብኒ እለ ጐዩ ውስተ ገዳም ተመይጥዎሙ ለእለ ዴገንዎሙ ፤

የጋይ ሰዎችም ወደኋላቸው ተመልሰው ባዩ ጊዜ ከሀገራቸው ጢስ ወደ ሰማይ አቅንቶ ሲወጣ አይተው ወደቀኝም ወደግራም ሁኖ የሚሸሹበት አጡ፤ ወደ ምድረ በዳ የሸሹትም ሰዎች የተከተሏቸውን ሰዎች ተመልሰው ወጓቸው ፤

፳፩፤ ወርእየ ኢያሱ ከመ ረከብዋ ለሀገር እለ ዐገትዋ ወእእመሩ ሰበ ርእዩ ጢሰ የዐርግ ውስተ ሰማይ እምሀገር ወእምዝ ተመይጡ እስራኤል ወቀተልዎሙ ለሰብአ ጋይ ፤

ኢያሱም ከበዋት የነበሩ ሰዎች ከተማዪቱን እጅ እንዳደረጓት አየ፤ ጢሱ ከከተማው ወደሰማይ አቅንቶ ሲወጣ ባዩ ጊዜ የጋይ ሰዎች አገራቸው እንደተያዘች አወቁ፤ ከዚያ በኋላ እስራኤል አግባ መልስ ብለው ተዋግተው የጋይን ሰዎች አጠፏቸው ፤

፳፪፤ ወእልክቱሂ ወፅኡ እምሀገር ወተቀበልዎሙ ወአግብእዎሙ ማዕከለ ትዕይንቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ወቀተልዎሙ ፤ ወእልክቱሂ እምከሀ ወእለሂ እምለፌ እስከ ኢያትረፉ እምኔሆሙ ነፋጺተ ዘድኅነ ፤

ድብቅ ጦር ሁነው ተቀምጠው የነበሩ ሰዎችም ከተሠወሩበት ቦታ ወጡ፤ እነዚያ በወዲያ፤ እነኢያሱ በወዲህ ሁነው በጠብ ተቀብለው በእስራኤል ሠፈር መካከል አግብተው ሽሽተኛ እንኳ ሳያስቀሩ አጠፏቸው ፤

፳፫፤ ወአኀዝዎ ለንጉሠ ጋይ ሕያዎ ወወሰድዎ ኀበ ኢያሱ ፤

የጋይንም ንጉሥ ሕይወቱ ሳለ ይዘው ወደ ኢያሱ ወሰዱት ፤

፳፬፤ ወሶበ አኅለቁ ቀቲሎቶሙ ለሰብአ ጋይ በገዳም ወበሙራደ ደብር ኀበ ዴገንዎሙ ወቀተልዎሙ ለኵሎሙ በሐፂን ወአጥፍእዎሙ ወተመይጠ ኢያሱ በጊዜሃ ውስተ ጋይ ወቀተለ በሰይፍ ፤

የጋይን ሰዎች በተከተሏቸው በምድረ በዳውና በቊልቊለቱ መውጋትን በጨረሱ ጊዜ ሁሉንም በጦር ወግተው ካጠፏቸው በኋላ ያን ጊዜ ኢያሱ ወደ ጋይ ተመልሶ ንጉሡን በሰይፍ መትቶ ገደለው ፤ ምነው አሰቀለው ይላሉሳ ቢሉ ሁሉም ተደርጓል በፊት በሰይፍ አስመትቶ ኋላ አሰቅሎታል ፤

፳፭፤ ወኮኑ ኵሎሙ ሰብአ ጋይ እለ ሞቱ ይእተ አሚረ ተባዕት ወአንስት ፲፻፸ ወ፳፻ተ ፤

ያን ጊዜ የሞቱት የጋይ ሰዎች ወንዶችም ሴቶችም ሁነው እልፍ ከሁለት ሺህ ናቸው ፤ (አንድም) አሥራ ሁለት ሺህ ናቸው ፤

፳፮፤ ወኢሜጠ ኢያሱ እዴሁ እንተ አልዓለ በጋይሶ እስከ አጥፍኦሙ ለሰብአ ጋይ ፤

ኢያሱ የጋይን ሰዎች እስኪያጠፋቸው ድረስ በጋሻው የጠቀሰበትን (ጦር የዘረጋበትን) እጁን አላጠፈም ፤

፳፯፤ ዘእንበለ እንስሳ ወበርበረ ሀገር ኵሉ ዘበርበሩ ደቂቀ እስራኤል

ለርእሰሙ፡ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለኢያሱ ፤

እግዚአብሔር ኢያሱን እንዳዘዘው የእስራኤል ልጆች ለራሳቸው ከከተማው ከዘረፉት ገንዘብና ከከብቱ በቀር እስኪአጨፉቸው ድረስ እጁን አላጠፈም ፤

፳፰፤ ወአውዓያ ኢያሱ ለሀገር በእሳት ወኮነት ሐመደ ወረሰያ ከመ አልቦ ዘያነብራ ለዘሉፉ እስከ ዛቲ ዕለት ፤

ኢያሱም አገሪቱን በእሳት አቃጠላት ፤ እሷም አመድ ትቢያ ሆነች ፤ እስከዚች ቀን ድረስ ለዘለዓለሙ የሚኖርባት እንዳይኖር አደረጋት ፤

፳፱፤ ወለንጉሠ ጋይ ሰቀሎ ዲበ ዕፀ ዘግባ ወነበረ ዲበ ዕፅ እስከ ሠርከ ወሶበ ዓርበ ፀሐይ አዘዘ ኢያሱ ያውርድዎ ፤

የጋይንም ንጉሥ በዘግባ እንጨት ላይ ሰቀለው ፤ እስከ ማታ ድረስ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ዋለ ፤ ፀሐይ ከገባ በኋላ ግን ኢያሱ አውርዱት ብሎ አዘዘ ፤

ወአውረድዎ እምዲበ ዕፅ ወወገርዎ ውስተ ግብ ቅድመ አንቀጸ ሀገር ወአንበሩ ላዕሌሁ አዕባነ አበይተ እስከ ዛቲ ዕለት ፤

ከእንጨት አውርደውም በከተማው አንፃር ባለ ጕድጓድ ውስጥ ጣሉት ፤ እስከዚች ቀን ድረስም ታላላቅ ደንጊያ ጫኑበት ፤

፴፤ ወነደቀ ኢያሱ ምሥዋዐ ይእተ አሚረ ለእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል በደብረ ጌባል ፤

ያንጊዜ ኢያሱ ጌባል በሚባል ተራራ ለእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ ፤

፴፩፤ በከመ አዘዞሙ ሙሴ ቀኍልዔሁ ለእግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል በከመ ጽሑፍ ውስተ ሕገ ሙሴ ምሥዋዐ ዘዕብን በመጥባሕት ዘኢተወቅረ ወዘኢተገብረ በሐፂን ወአዕረገ ቍርባነ ወመሥዋዕተ መድኃኒት ለእግዚአብሔር ፤

የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ የእስራኤልን ልጆች እንዳዘዛቸው በሙሴ መጽሐፍ በዳግም ሕግ እንደተጻፈ በመጥረቢያ ባልተጠረበ በብረትም ባልተቀረጸ (ባልለዘበ) መሠዊያ ላይ የድኅነት መሥዋዕትና ቍርባንን ለእግዚአብሔር አቀረበ ፤

፴፪፤ ወጸሐፎ ኢያሱ ውስተ አዕባን ለዳግም ኦሪት ዘጸሐፈ ሙሴ በቅድሜሆሙ ለኵሉ ደቂቀ እስራኤል ፤

ኢያሱም ሙሴ በእስራኤል ልጆች ፊት የጻፈው ዳግም ሕግን በደንጊያ ላይ ጻፈው (ቀረጸው) ፤

፴፫፤ ወኵሉ እስራኤል ወመኳንንቲሆሙ ወጸሐፍቶሙ ይቀውሙ እምየማን ወእምጺጋም ቅድመ ታቦት

ወካህናትሰ ወሌዋውያን ይፀውሩ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር ፤

**እስራኤል ሁሉና መኳንንቱ ሹማምንቱም ሁሉ ሁነው በታቦተ ጽዮን ፊት በቀኝ በግራ ሁነው ቁመው ነበር ፤ የሌዊ ወገኖች ካህናቱ ግን የእግዚአብሔር የሕጉ ማደሪያ ታቦትን ተሸክመው በመካከል ቁመው ነበር ፤**

ወመንፈቆሙ ለግዩራን ወእለሂ እም ፍጥረቶሙ መንፈቆሙ ጥቃ ደብረ ገሪዛን እለ አዘዞሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር ከመ ይባርክዎ ለሕዝበ እስራኤል ወእሙንቱሂ ይቀውሙ ፤

**ከመጻተኞችም፣ ፍጥረታቸው እስራኤል ከሆኑትም ወገን የእግዚአብሔር ወዳጅ ሙሴ ያዘዛቸው የእስራኤልን ወገኖች ይመርቋቸው ዘንድ እኩሌቶቹ በጌባል ፤ እኩሌቶቹ በገሪዛን አጠገብ ቁመው ነበር ፤**

፴፬፤ ወእምድኅረ ዝንቱ አንበበ ኢያሱ ኵሎ ነገሮ ለዝንቱ ሕግ በረከቶሂ ወመርገሞሂ ኵሎ ዘጽሑፍ ውስተ ሕገ ሙሴ ፤

**ከዚህ በኋላ ኢያሱ የዳግም ሕግን ነገር በሙሴ መጽሐፍ የተጻፈውን በረከቱንም መርገሙንም ሁሉ አነበበላቸው ፤**

፴፭፤ ወአልቦ ቃል እምኵሉ ዘአዘዞ ሙሴ ለኢያሱ ዘኢያንበበ ወዘኢያስምዖሙ ኢያሱ ለኵሉ ተዓይነ ደቂቀ እስራኤል ለዕደዊሆሙ ወለአንስቲያሆሙ ወለደቂቆሙ ወለግዩራን እለ ሖሩ ምስለ እስራኤል ፤

**ሙሴ ለኢያሱ ካዘዘው ትእዛዝ ሁሉ ኢያሱ ለእስራኤል ልጆች ለወንዶችና ለሴቶች ከእስራኤል ጋር ለሔዱ መጻተኞችና ለልጆቻቸውም ያላነበበላቸውና ያላሰማቸው ቃል የለም ።**

## ምዕራፍ ፱

፩፤ ወሶበ ሰምዑ ኵሎሙ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ህለዉ በማዕዶተ ዮርዳኖስ እለ ውስተ አድባር ወእለ ውስተ ገዳም ወእለ ውስተ ኵሉ ሐይቀ ባሕር ዓቢይ ወእለ ውስተ አንጢሊባኖን ፤

**በዮርዳኖስ ማዶ በደጋም በቈላም በደሴትና በባሕር አጠገብ ያሉ የአሞሬዎን ነገሥታት ሁሉ ፤**

ወኬጤዎን ወከናኔዎን ወፌርዜዎን ወኤዌዎን ወአሞሬዎን ወጌርጌሴዎን ወኢያቡሴዎን ፤

**እነዚህ ሰባቱ ነገሥታተ አሕዛብ ይህን በሰሙ ጊዜ ፤**

፪፤ ተጋብኡ ኅቡረ ከመ ይጽብእዎሙ ለኢያሱ ወለኵሉ እስራኤል ፤

**ኢያሱንና እስራኤልን ይወጓቸው ዘንድ በአንድነት ተሰበሰቡ ፤**

፫፤ ወሰምዑ እለ ይነብሩ ውስተ ገባዖን ኵሎ ዘገብረ እግዚአብሔር ላዕለ ኢያሪኮ ወላዕለ ጋይ ፤

በገባዖን የሚኖሩ ሰዎች ግን እግዚአብሔር በኢያሪኮና በጋይ ላይ ያደረገውን ሁሉ ሰም ተው ፤

፬፤ ወገብሩ እሙንቱሂ በጕሕሉት ወመጽኡ ሰነቂቆሙ ወአስተዳሊዎሙ ወፆሩ መሳንቅቲሆሙ ብሉያተ ዲበ መታክፍቲሆሙ ወዝቃቀ ወይን ብሉያተ ወሥጡጣተ ወጥቁባተ ፤

እነሱም ተንኰል አድርገው ስን ቃቸውን ሰንቀው አዘጋጅተው፤ ያረጀ አቅማዳቸውን በጫንቃ ቸው ተሸክመው ፤ ያረጀ ተቀዶ የተጣፈውን የወይን ረዋት ይዘው መጡ ፤

፭፤ ወብቱክ ቶታነ አሣዕኒሆሙ ወብ ሉይ አሣዕኒሆሙ ወግቱት ውስተ እገሪሆሙ ወአልባሲሆሙኒ ብሉይ በላዕሌሆሙ ወኅብስተ ስንቆሙኒ ይቡስ ወስህቡብ ፤

የጫማቸው ማዘቢያ ተቆርጦ ጫማቸው አርጅቶ የተገተተ ሁኖ በበላያቸው ያለ ልብሳቸ ውም ያለቀ ሁኖ የደረቀና የሻ ገተ ዳቦ ስንቅ ይዘው መጡ ፤

፮፤ ወመጽኡ ኀበ ኢያሱ ውነበ እስ ራኤል ውስተ ገልገላ ወይቤልዎሙ ለኢያሱ ወለኵሉ ደቂቀ እስራኤል እምርኁቅ ብሔር መጻእነ ወይእዜኒ ተማሐሉ ምስሌነ ፤

ከኢያሱና ከእስራኤል ዘንድ ወደገልገላ መጥተው ኢያሱን፤ እስራኤልን፤ ከሩቅ አገር መጥ ተናልና እንዲታጠፉን ማሉልን አሏቸው ፤

፯፤ ወይቤልዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለኤዊያውያን እፎ ንትማሐል ምስ ሌክሙ መሐላ ሁቁ ዮጊ ቅሩባነ ትነብሩ ፤

የእስራኤልም ልጆች የገቦአንን ሰዎች ከናንተ ጋር እንደምን እንማማላለን ወይም እንጂ ከቅ ርብ አገር መጥታችሁ ይሆናል አሏቸው ፤ እንድም የመጣችሁ ከቅርብ እንዳይሆን እነሆ ለራ ሳችሁ እወቁ አሏቸው ፤

፰፤ ወይቤልዎ ለኢያሱ ንሕነሰ አግ ብርቲከ እምርኁቅ ብሔር ንሕነ ወይ ቤሎሙ እምአይቴ አንትሙ ወእም አይቴ መጻእክሙ ፤

ኢያሱን እንዲህ አሉት ፤ እኛ ባሮችህ ከሩቅ አገር የመጣን ነን አሉት ፤ እሱም ከወዴት ናችሁ ከወዴትስ መጣችሁ አላቸው ፤

፱፤ ወይቤልዎ እምርኁቅ ብሔር ጥቀ መጻእነ ንሕነ አግብርቲከ በስመ እግዚአብሔር አምላክከ እስመ ሰማ

ዕነ ዘበእንተ ኵሉ ዘገብረ በግብጻውያን ፤

እኛ ባሮችህ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ስም አምነን እጅግ ከራቀ አገር መጥተናል አሉት፤ እግዚአብሔር በግብጻውያን ያደረገውን ነገር ሁሉ ሰምተናልና ፤

፲፡ ወኵሎ ዘገብረ በ፪ኤቱ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ ማዕዶተ ዮርዳኖስ በሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን ወበዓግ ንጉሠ ባሳን ዘይነብር ውስተ አስጣሮት ወውስተ ኢንድራይን ፤

በዮርዳኖስ ማዶ በሚኖሩ በሁለቱ የአሞሬዎን ነገሥታት በሐሴቦን ንጉሥ በሴዎንና በአስጣሮት በኢንድራይን በሚኖር በባሳን ንጉሥ በዓግ ያደረገውንም ሰምተናል ፤

፲፩፡ ወይቤሉነ ሊቃናቲነ ወኵሉ ሰብአ ብሔርነ ንሥኡ ስንቀ ለፍኖት ወሑሩ ትትቀበልዎሙ ወበልዎሙ አግብርቲክሙ ንሕነ ወይእዜኒ ተማሐሉ ምስሌነ ፤

አለቆቻችንና የሀገራችን ሰዎች ሁሉ ለመንገድ የሚሆናችሁ ስንቅ ይዛችሁ ትቀበሏቸው ዘንድ ሒዱ ፤ እኛ አገልጋዮቻችሁ (ባሮቻችሁ) ነን ፤ ነገና አሁንም እንዲታጠፉን ማሉልን በሏቸው አሉን ፤

፲፪፡ ወናሁ ዝንቱ ኅብስትነ እንዘ ምውቅ ውእቱ ነሣእናሁ እምአብያቲነ በዕለተ ወፃእነ ከመ ንምጻእ ኀቤክሙ ወይእዜሰ ነቅዘ ወየብሰ ፤

ወደናንተ እንመጣ ዘንድ ከቤታችን በወጣንበት ቀን ትኩሱን የያዝነው ይህ ስንቃችን እነሆ ሻገተ ደረቀ ፤

፲፫፡ ወዝንቱኒ ዝቀ ወይን ዘመላእናሁ ሐዲሰ ይእዜሰ ዓረቀ ወበልየ ወተሠጠ ፤

ይህም የወይን ረዋት አዲሱን የወይን ጠጅ መላነው ዛሬ ግን ተራቆተ አርጅቶም ተቀደደ ፤

ወዝንቱኒ አልባሲነ ወአሣዕኒነ በልየ እስመ ጥቀ ርኁቅ ፍኖትነ ፤

መንገዳችን እጅግ የራቀ ነውና አዲሱ ጫማችንና ልብሳችን አረጀ አላቸው ፤

፲፬፡ ወነሥኡ መኳንንት ስንቆሙ ወኢተስእሉ በኀበ እግዚአብሔር ፤

መኳንንቱም ስንቃቸውን ተቀብለው አይተው ቃለ እግዚአብሔር ሳይጠይቁ አመኗቸው ፤ (ሐተታ) አያየዝ የማታውቅ ሴት የጋገረችው ዕለቱን እንዲሻግት እንዲሉ ባያውቁ ፤

፲፭፡ ወገብረ ኢያሱ ሰላመ ምስሌሆሙ ወተማሐለ ምስሌሆሙ ከመ ያድኅኖሙ ወመሐሉ ሎሙ መላእክተ ተዓይን ፤

ኢያሱም ከሰብአ ገባዖን ጋር ፍቅር አንድነት አደረገ ከጥፋት

ያድናቸውም ዘንድ ከነሱ ጋር ተማማለ የሠራዊቱ አለቆችም አገራችሁ ሩቅ ከሆነ አናጠፋ ችሁም ብለው ማሉላቸው ፤

፲፮፤ ወእምድኅረ ሠሉስ መዋዕል እምድኅረ ተማሐሉ ምስሌሆሙ መሐላ ሰምዑ ከመ እምቅሩብ እሙ ንቱ ወከመ ነቢሆሙ እሙንቱ ይነ ብሩ ፤

ከእነሱ ጋራ መሐላን ከተማማሉ ከሦስት ቀን በኋላ አገራቸው ቅርብ እንደሆነ ባጠገባቸውም እንዲኖሩ ሰሙ ፤

፲፯፤ ወግዕዙ ደቂቀ እስራኤል ወበ ጽሑ ውስተ አህጉሪሆሙ አመ ሣል ስት ዕለት ወእላንቱ እማንቱ አህጉ ሪሆሙ ገባዖን ወፈራ (ፋራን) ወቤ ሮት ወኢያርም ፤

የእስራኤል ልጆችም ተጉዘው በሦስተኛው ቀን ከሰብአ ገባኦን አገር ደረሱ ፤ አገሮቻቸውም ገባዖን ፤ ፋራን ፤ ቤሮት ፤ ኢያ ርም እነዚህ አራቱ ናቸው ፤

፲፰፤ ወኢቀተልዎሙ ደቂቀ እስራ ኤል እስመ መሐሉ ሎሙ ኵሎሙ መላእክተ ተዓይን በእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፤

የሕዝቡ አለቆች በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ስም ምለ ውላቸዋልና የእስራኤል ልጆች አላጠፏቸውም ፤

ወአንጐርጐሩ ኵሉ ተዓይኒሆሙ ለደቂቀ እሥራኤል ላዕለ ኵሉ መላ እክቲሆሙ ፤

የእስራኤል ወገኖች ሁሉ ባለቆ ቻቸው ላይ አንጐራጐሩ ማለት አዘኑ ተበሳጩ ፤

፲፱፤ ወይቤልዎሙ ኵሉ መላእክት ለኵሉ ተዓይን ንሕነ መሐልነ ሎሙ በእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ወይእዜኒ ኢንክል ለኪፎቶሙ ወኢበ ምንትኒ ፤

አለቆቹ ሁሉ ሕዝቡን እንዲህ አሉዋቸው እኛ በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ስም ምለንላቸዋልና አሁንም መሐ ላውን አፍርሰን በምንም በምን እነሱን ማጥፋት አንችልም ፤

፳፤ ወባሕቱ ከመዝ ንግበር ናሕይ ዎሙ ወንቅንዮሙ ወኢይከውን ላዕሌነ መንሱት በበይነ ዘመሐልነ ሎሙ ፤

ነገር ግን እንዲህ እናድርግ በእ ግዚአብሔር ስም ስለማልንላ ቸው በኛ ጥፋት እንዳይመጣ ብን ከሞት አድነን እንግዛ ቸው ፤

፳፩፤ ወይቤልዎሙ መላእክት አሕዮ ናከሙ ወሢምናከሙ ትሕጥቡ ዕፀወ ወትቅድሑ ማየ ለኵሉ ተዓይን ወከመዝ አዘዝዎሙ መላእክት ፤

አለቆቹም እንዲህ አሏቸው ፤ ለሠፈሩ ሁሉ ማለት ለቤተ እግ

ዚአብሔር እንጨት ሰባሪ ውሃ ቀጅ ሆናችሁ ትኖሩ ዘንድ ከሞት አድነን ሹመናችኋል አሉ አቸው ፤ እንዲህም ብለው አለ ቆቹ አዘዙዋቸው ፡

፳፪፤ ወጸውአሙ ኢያሱ ወይቤሎሙ ለምንት ተሳለቅሙ ላዕሌነ ወትቤሉነ ርኁቃን ንሕነ ጥቀ እምኔክሙ ወናሁ አንትሙ ትነብሩ ውስቴትነ ፤

ኢያሱም ጠርቶ ከናንተ እጅግ የራቅን ነን ብላችሁ ለምን ዘበ ታችሁብን ? እነሆ እናተ በአጠ ገባችን ትኖራላችሁ እንዲህ ስት ሆኑ ለምን ዘበታችሁብን ፤

፳፫፤ ወይእዜኒ ርጉማን ኩኑ ወኢ ይሠዓር እምኔክሙ ገብር ዘየሐጥብ ዕፀ ወዘይቀድሕ ማየ ለአምላኪየ ወሊተኒ ፤

አሁንም የተረገማችሁ ሁኑ ፤ ከናንተ ወገን ለፈጣሪዬና ለኔ (ለቤተ እግዚአብሔርና ለቤተ መንግሥት) እንጨት የሚለ ቅም ውሃ የሚቀዳ አገልጋይ ከናንተ አይታጣ አላቸው ፤

፳፬፤ ወአውሥእዎ ወይቤልዎ ዜና ዜነዉነ ኵሉ ዘይቤሎ እግዚአብ ሔር አምላክከ ለሙሴ ቍልዔሁ ከመ የሀብክሙ ዛተ ምድረ ፤

እነሱም መለሱለት ፤ እንዲህ አሉት ፤ ይኸችን ምድር ይሰጣ ችሁ ዘንድ ፈጣሪህ እግዚአብ ሔር ለባለሟሉ ለሙሴ የነገ ረውን ነገር ሁሉ ሰማን ፤

ወከመ ያጥፍአነ ለነ ወለኵሉሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ እምቅድመ ገጽክሙ ወበበይነ ዝንቱ ገበርነ ዘንተ ነገረ ፤

እኛንም በውስጧ የሚኖሩት ንም ሰዎች ሁሉ ከፊታችሁ እንዲያጠፉን ነገሩን ስለዚህም ይህን ነገር አደረግን ፤

፳፭፤ ወይእዜኒ ናሁ ንሕነ ውስተ እዴክሙ ዘከመ ፈቀድክሙ ወዘ ከመ ይኤድመክሙ ትረስዩነ ረስ ዩነ ፤

አሁንም እነሆ እኛ በእጃችሁ የተያዝን ነን እንደወደዳችሁ ደስ እንደሚያሰኛችሁ ታደር ጉን ዘንድ የወደዳችሁትን አድ ርጉ አሉት ፤

፳፮፤ ወአድኀኖሙ ኢያሱ በይእቲ ዕለት ፤

ኢያሱም በዚያች ቀን ከሞት አዳናቸው ፤

፳፯፤ ወረሰዮሙ ከማሁ ሐጣብያነ ዕፀው ወሐዋርያነ ማይ ለምሥዋዓ እግዚአብሔር ወለኵሉ ተዓይን እስከ ዛቲ ዕለት ፤

አሁን እንደተናገርነው ከሞት አድኖ እስከዚች ቀን ድረስ ለቤተ እግዚአብሔር ፤ ለቤተ መንግሥት እንጨት ሰባሪዎች፤ ውሃ ቀጂዎች አደረጋቸው ፡፡